# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 83ኛ ዓመት ቁጥር 254 ግንቦት 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# ለቱሪዝም ምቹ ዕድል የሚፈጥረው ጽዱ ኢትዮጵያ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

**ዜና ትንታኔ**

"ጽዱ ከተሞች ለኢትዮጵያ ከፍታ" በሚል መሪ ሃሳብ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄድ የከተሞች ጽዳትና የአረንጓዴ ልማት ንቅናቄ መካሄድ ከጀመረ ቀናት ተቆጥረዋል። በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በተካሄደ ጽዱ ኢትዮጵያ ዲጅታል ቴሌቶን በአንድ ቀን 40 ሺ 533 ሰዎች ተሳታፊ ሆነው 154 ሚሊዮን 500ሺ ብር ተሰብስቧል።

በዚህ እንቅስቃሴ እስከ ክረምት መግቢያ የኮሪዶር ልማትን ጨምሮ በርካታ የችግኝ ተከላና የከተማ ጽዳት የሚከናወን መሆኑም ተመላክቷል። የጽዱ ኢትዮጵያ ተግባራዊ መሆን ከተሞችን ውብ፣ ለነዋሪዎች ጤናማ ሁኔታን ከመፍጠር ባለፈ ለሀገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ የሚያበረክተው የራሱ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ከፍተኛ የቱሪዝም ተመራማሪና መምህር የሆኑት አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) ለቱሪዝም አለማደግ እንደ አንድ ምክንያት የሚጠቀሰው የጽዳት ጉዳይ መሆኑን በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴና በደርግ ዘመነ

ለቱሪዝም ምቹ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ

## ከሀገር ውስጥ ጎብኚዎች 48 ነጥብ ስምንትቢሊዮን ብር በኢኮኖሚው ተንቀሳቅሷል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ከሀገር ውስጥ ጎብኚዎች 48 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በኢኮኖሚው መንቀሳቀሱን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ። የቱሪዝም ዘርፉ ለኢኮኖሚው የሚጠበቅበትን ድርሻ እንዲያበረክት አስቻይ ሁኔታዎችን

ከሀገር ውስጥ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ግርማ አመንቴ(ዶ/ር)

## 12 ነጥብ 1 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ተጓጉዞ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቷል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ግብርና ሚኒስቴር 12 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ተጓጉዞ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱን ገለጸ።

ሚኒስቴሩ የ2016 በጀት ዓመት የ10 ወራት የፌዴራልና

12 ነጥብ 1 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢትዮጵያ የቻይና-አፍሪካ

## የልማት ትብብር እንዲጠናከር የምታበረክተውን አስተዋጽኦ ትቀጥላለች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የቻይና-አፍሪካ የልማት ትብብር ይበልጥ እንዲጠናከር የምታደርገውን አስተዋጽኦ አጠናክራ እንደምትቀጥል ተገለጸ።

በቻይና-አፍሪካ ትብብር ፎረም ኢትዮጵያ እንደ አፍሪካዊ ወካይ ድምፅ የነበራት የመሪነት ሚና ከትናንት እስከ ዛሬና ቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ የከፍተኛ ባለሙያዎች ጉባኤ ትናንት ተካሂዷል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ኃላፊ አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን በወቅቱ እንደተናገሩት፤ የቻይና የልማት መርሀ ግብሮች ከአፍሪካ የልማት አጀንዳ ጋር ተጣጥመው የሚሄዱ መሆናቸውን አንስተው፤ ኢትዮጵያም የልማት ትብብሩ እንዲጠናከር ድጋፏን ለማጠናከር ትሠራለች።

አፍሪካ የእርስ በእርስ ግጭት፣ ወረርሽኝ፣ ድህነትና በርካታ ችግሮችን እያስተናገደች መሆኑን ገልጸው፤ በትብብር መሥራት እንደሚገባ ጠቁመው፤ በመሠረተ ልማት፣ በአቅም ግንባታ፣ በግብርናና በሌሎች የትብብር መስኮችን በጋራ በመሥራት የአፍሪካ ማህበራዊና ምጣኔ

. ኢትዮጵያ የቻይና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን



ያንግ ይሀንግ

ፎቶ - ዳኜ አበራ






ወይዘሮ ሙና አሕመድ

# ጥምረቱ የወጣቶች ተጠቃሚነትን ይበልጥ ለማሳደግ ያግዛል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በወጣቶች ጉዳይ የሚሠሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጥምረት መመስረቱ የወጣቶችን ተጠቃሚነት ይበልጥ ለማሳደግ እንደሚያግዝ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በወጣቶች ዙሪያ የሚሠሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጋራ ፎረም ስምምነቱን በመዲናዋ ተመስርቷል።

በወቅቱ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሙና አሕመድ እንደገለጹት፤ ጥምረቱ በተደመረ አቅም ለውጥ በማምጣት የወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ለማረጋገጥ ያለመ ነው፡፡

ወጣቶች በየዘርፉ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ደረጃ በደረጃ በመቅረፍ ለራሳቸውና ለሀገራቸው ሁለንተናዊ እድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል በመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በተናጠል በርካታ ሥራዎች መሥራታቸውን ጠቁመዋል። በተጻራሪው ደግሞ ከቆሙለት አላማ ውጪ ለግል ጥቅማቸው የሚሠሩ ድርጅቶችም ነበሩ ሲሉ አንስተዋል።

ጥምረቱ መመስረቱ ተቋማቱ በፕሮግራሞቻቸው ውስጥ ወጣቱን በተገቢው መልኩ አካተው እንዲሠሩ፣ በመንግሥትና በአጋር አካላት መካከል ትብብርና ቅንጅትን ለማጠናከር፣ ሀብትን በጋራ ለማሰባሰብ እንዲሁም የወጣቱን ችግር በጋራ በመፍታት ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ይረዳል ሲሉ አስረድተዋል።

የሀገሪቷ የወደፊት እጣ ፈንታ የሚወሰነው በወጣቶች ስኬት ላይ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በወጣቶች ላይ ኢንቨስት በማድረግ ፣ ለሥራ ፈጠራ፣ የሙያ ስልጠናና ዕድገት በሮችን በመክፈት ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

በተጨማሪም ለወጣቶች ስብዕና ግንባታ እንዲሁም አካላዊና አዕምሯዊ ጤንነት ትኩረት መስጠት እንደሚገባ አንስተው፤ ለዚህም ወጣቶች ከሱስና አሉታዊ ልማዶች እንዲጠበቁ የመከላከል ሥራዎችን ማከናወንና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤዎችን ያካተቱ ወጣት ተኮር አሠራሮችን ቀርጾ መተግበር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

ለዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በራሱ ከሚሠራው ሥራ በተጨማሪ በወጣቶች ዙሪያ ከሚሠሩ አጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታዋ አመላክተዋል።

እንደ ወይዘሮ ሙና ገለጻ፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አዳዲስ የልማት ውጥኖች ለወጣቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት መጎልበት ምቹ እንዲሆኑ የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ የሕግና የአሠራር ሥርዓቶችን በመቅረጽ እንዲሁም በማሻሻል ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመሆን እየሠራ ይገኛል።

# ለሀገር ኩራት የመሆን ዝግጁነት - በብላቴ

**ጌትነት ተስፋማርያም**



በአካባቢው ከፍተኛ ወበቅ አለ። በማሰልጠኛው ባለግማሽ ክብ ቅርጽ ያላቸው ሰፋፊ ቤቶች እዚህም እዚያም ይታያሉ። በእነዚህ ማደሪያዎች ውስጥ ደግሞ ሙቀቱን ተቋቁመው የኮማንዶ ስልጠና የሚወስዱ ወጣቶች ይኖሩባቸዋል።

ማዕከሉን አቋርጦ ከሚያልፈው ወንዝ ስሙን ያገኘው ብላቴ የኮማንዶና አየር ወለድ ማሰልጠኛ ለነዚህ ወጣቶች የዕውቀትና ክህሎት ቤታቸው ነው። በግቢው የሥራ ባህል መሠረት ሌሊት 10 ሰዓትና ከዚያም በፊት ቀድመው የሚጀመሩ ስልጠናዎች የተለመዱ ናቸው።

የአካል በቃት እንቅስቃሴ ያደረጉ ሰልጣኞች ፊታቸው ላይ ላብ ይንቆረቆራል። በስልጠናው መስፈርት አሟልተውና ተፈትነው ያለፉ አሰልጣኞች ደግሞ በየዙሩ ለሚገቡ ወጣቶች ተገቢውን ክህሎትና ዕውቀት አስጨብጠው መላኩን ዛሬም አልቦዘኑም። ከእነዚህ ሰልጣኞች መካከል ደግሞ የመከላከያ ሠራዊት አባሏ 50 አለቃ ጽጌ አሰፋ አንዷ ነች።

በብላቴ ለሴት ወይም ለወንድ ተብሎ የተለየ የአካል ብቃት የለም፤ እኔም ከወንዶች እኩል ብቻ ሳይሆን አንዳንዴም ከወንዶች በላይ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ስልጠናዎችን አጠናቅቄ ተመርቄያለሁ ስትል ቆይታዋን ታስረዳለች።

ወታደራዊ ሳይንስ ስልጠናዎች በተገቢው መንገድ ወስደናል የምትለው 50 አለቃ ጽጌ፤ በአስገምጋሚው ብላቴ ወንዝ ላይ የተደረጉ በገመድ ላይ ተንጠልጥሎ መጓዝ፣ አለት የመውጣትና የተለያዩ ፈታኝ የኮማንዶ ስልጠናዎችን እንስቶች በብቃት መወጣት እንደምንችል አሳይተናል ብላለች።

በወሰድኳቸው የውጊያ ቴክኒኮችና የተለያዩ የአካልና የአዕምሮ ስልጠናዎች አማካኝነት ብቃቴን አሳድጌያለሁ፤ በቀጣይም ሀገሬንና ሕዝቤን በተሻለ መንገድ ለማገልገል ዝግጁ ነኝ ስትል ተናግራለች።

በፀጥታው ዘርፍ ተሰልፌ ኢትዮጵያን ማገልገል ቀድሞም የምመኘው ነገር ነበር፤ አሁን ደግሞ የተሻለ የኮማንዶ ስልጠና ወስጄ አቅሜን አሳድጌያለሁ የምትለው ደግሞ የፌዴራል ፖሊስ አባሏ ኮንስታብል ነፃነት ተረፈ ነች።

በርካታ እንስቶች የኮማንዶና አየር ወለድ ስልጠናን ከወንዶች እኩል እንዴት ይፈጽሙታል የሚል ጥርጣሬ ያላቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ የምትለው ኮንስታብል ነፃነት፤ በርካቶች ግን በተግባር ብቃታቸውን አሳይተው በልዩነት የሚሸለሙበት ጊዜም እንዳለ ነው የምትገልጸው።

ሀገርን በተሻለ አቅም ለማገልገል የኮማንዶ ስልጠናው ወሳኝ መሆኑን አንስታ፤ በማንኛውም የአየር ንብረትና በተለያየ የመሬት አቀማመጥ የማይበገር ፣ በፀረ ሽብር ሥራዎች ውጤት ለማስመዝገብና በገባችበት ቀጣና ሁሉ አኩሪ ገድል ለማስመዝገብ የሚያስችል ስልጠና እንዳገኘች ነግራናለች።

መሠረታዊ ወታደር ሙባረክ አወል በበኩሉ ፤ ብላቴ ዘመኑ የሚፈልገውን ክህሎት ያሟሉ ታታሪ አሰልጣኞች መኖራቸውንና ለኮማንዶነት የሚያስፈልገውን በቂ ጊዜ ወስደው ስልጠና መውሰዳቸውን ነው የተናገረው።

እንደ ወታደር ሙባረክ ከሆነ፤ የ42ኛ ዙር ኢትዮጵያ ኮርስ ሰልጣኝ መሆኑን አስታውሶ፤ ሰልጣኞች በኮማንዶ የመመረቂያ መስፈርቶች መሰረት በችሎታ፣ በዕውቀት፣ በአስተሳሰብና በባህሪ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ እንዲወጡ የሚያስችል ስልጠናና የብቃት ፈተና ተሰጥቷል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ማሰልጠኛዎች ውስጥ በቂ ትምህርት አግኝተን የምንወጣ የኢትዮጵያ ልጆች ነገ በአስፈላጊው ጊዜ ለኢትዮጵያ ሰላምና ዳር ድንበር መከበር እስከ ሕይወት መስዋዕትነት የሚደርሱ ግዳጆችን ለመፈጸምና የሀገር ኩራት ለመሆን ዝግጁ ነን ሲልም ሃሳቡን ሰጥቷል።

በኮማንዶና አየር ወለድ ማሰልጠኛ ማዕከላት ፀሐይና ብርዱን እንዲሁም የጎርፍ ወጀቡን ተቋቁመው በፈተና የሚያልፉ ተመራቂዎች እንዳሉ ሁሉ፤ ከጀርባ ሆነው ደግሞ ውድ ልጆችን እያፈሩ የሚገኙ ብቃት ያላቸው በርካታ አሰልጣኞችም በመኖራቸው ለእነሱም ክብር አለን ሲሉ ተመራቂዎቹ ለአሰልጣኞቻቸውም ምስጋና አቅርበዋል።

# አውደ ርዕዩ አካል ጉዳተኞች በጥራት ማምረት እንደሚችሉ ተጨባጭ ማሳያ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአምራች አካል ጉዳተኞች የተዘጋጁ የተለያዩ የእጅ ሥራ ውጤቶች የቀረቡበት አውደ ርዕዩ አካል ጉዳተኞች በጥራት ማምረት እንደሚችሉ ተጨባጭ ማሳያ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ገለጸ፡፡

ቢሮው "አካል ጉዳተኞች መሥራት ይችላሉ!" በሚል መሪ ሃሳብ ያዘጋጀው አወደ ርዕይ ትናንት ተከፍቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ወይንሸት ዘሪሁን በመርሀ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ የተዘጋጀው ባዛር አካል ጉዳተኞች አይችሉም የሚለውን የተሳሳተ እሳቤ በመቀየር ጥራት ያላቸውን ምርቶች ማዘጋጀት እንደሚችሉ ማሳያ ነው፡፡

ለአካል ጉዳተኞች አካታች በሆነ ዕውቀትና ክህሎት ከበለጸጉ እንዲሁም መሥራት የሚችሉበት ምቹ ምህዳር ከተፈጠረላቸው ከሌላው እኩል የማምረት ብቃት እንዳላቸው አውደ ርዕዩ በቂ ማስረጃ መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪም አውደ ርዕዩ ተሳታፊ አምራች አካል ጉዳተኞች ለሌሎች ተምሳሌትና አርዓያ ሆነው አንችልም የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ያላቸውን ዜጎች እሳቤ መቀየር የሚያስችል አጋጣሚን ይፈጥራል ብለዋል።

በየቤቱ የተደበቁትን ለማብቃት ተመሳሳይ አውደ ርዕዮች አስፈላጊ መሆናቸውን አንስተው፤ የተዘጋጀው አውደ ርዕይ አካል ጉዳተኞች እራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውን ብሎም ሀገራቸውን በኢኮኖሚያዊ ምርታማ የማድረግ ብቃት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ መሆኑን አስረድተዋል።

በአውደ ርዕዩ በመዲናዋ የሚገኙ 50 አምራች የአካል ጉዳተኞች ምርታቸውን የሚያስተዋውቁበትና የገበያ ትስስር የሚፈጥሩበት መሆኑን አመላክተው፤ ከነዚህም መካከል 14ቱ አምራቾች ከሦስት እስከ 11 አባላት ይዘው የተደራጁ ማህበራት ሲሆኑ፤ 16ቱ



በአውደ ርዕዩ በአምራች አካል ጉዳተኞች የተዘጋጁ ምርቶች ቀርበዋል

ደግሞ የግል አምራቾች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ የተቀሩት ደግሞ በተለያየ መንገድ የተሰባሰቡ አምራቾች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የቢሮው የማህበራዊ ዘርፍ ኃላፊ ወይዘሮ ገነት ቅጣው በበኩላቸው፤ ቢሮው በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት አካል ጉዳተኞችን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባራት ተሳታፊና ተጠቃሚ የማድረግ ኃላፊነት አለበት ብለዋል።

አላማውን ለማሳካት ለአምራች አካል ጉዳተኞች የተዘጋጀው አውደ ርዕይ በኢኮኖሚያዊ መንገድ ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆኑን አመላክተዋል።

አውደ ርዕዩ በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰነዘሩ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን በማስተካከል ውጤታማ መሆን እንደሚችሉና ከራሳቸውም አልፎ ለብዙኃኑ መጥቀም እንደሚችሉ የሚያረጋግጡበት መሆኑን ገልጸዋል።

ቢሮው አካል ጉዳተኞች ይበልጥ እንዲያመርቱ የሚረዱ የሙያ ስልጠናዎችን በማቅረብ ፣ የማምረቻና የመሥሪያ ቦታ በማመቻቸት እንዲሁም ምርታቸውን በማሳየት የገበያ ዕድል እንዲያገኙ የሚሠራውን ሥራ አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

ማህበረሰቡም በተመጣጣኝ ዋጋ ጥራት ያላቸውን ምርቶች በመግዛት አካል ጉዳተኞችን በማበረታታትና በመደገፍ የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ትናንት የተከፈተው አውደ ርዕይ በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ አካባቢ የተዘጋጀ ሲሆን፤ እስከ ግንቦት 17 ቀን 2016 እንደሚቆይ ታውቋል።

በአውደ ርዕዩ በአምራቾች አካል ጉዳተኞች የተዘጋጁ የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችና አልባሳት፣ እደ-ጥበብና የባልትና ውጤቶች ለገበያ ቀርበዋል።

# የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር 300 ለሚጠጉ የመዲናዋ ወጣቶች ስልጠና ሰጠ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር 300 ለሚጠጉ የመዲናዋ ወጣቶች በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በኢኖቬሽን ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጠ።

ስልጠናውን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ሲሆን፤ ይህም ለሁለት ቀናት ሲሰጥ ቆይቶ ትናንት ተጠናቋል።



የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ባይሳ በዳዳ (ዶ/ር)፤ በስልጠናው የማጠቃለያ ንግግር እንዳሉት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወጣቶችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። ይህም የቴክኖሎጂ ሥነ ምህዳር የማስተካከል፣ በቂ ቤተ ሙከራዎች (ላቦራቶሪዎችን) የማዘጋጀት፣ የኢንተርኔት እና መሰል መሠረተ ልማቶች ማሟላት ተጠቃሽ ናቸው።

በዚህም የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ወጣቶች ለማገዝ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። ይህም የገንዘብ፣ የቁሳቁስ እና የእውቀት ድጋፍ መሆኑን ጠቁመው፤ መንግሥት ለሀገራዊ ልማቱ መቀላጠፍ የፈጠራና የቴክኖሎጂ ተግባራትን የሚደግፍና ለውጤት የሚያበቃ አሠራር በፖሊሲ ደግፎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ብለዋል።

ይህም በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሽግግር እንዲኖር ያስችላል። እውቀት ኖሯቸው ሀብት የሌላቸውን በማገዝ ለውጤት እንዲበቁ የማድረግ ሥራዎች በመሠራት ላይ መሆናቸውን አመልክተው፤ ወጣቶች ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ እንደሚገባ ተናግረዋል።

የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በሚመለከት ለወጣቶቹ ስልጠና የሰጡት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የዲጂታል ማህበረሰብ ስፔሻሊስት አቶ በኃይሉ ዘውዱ በበኩላቸው፤ አብዛኞቹ ወጣቶች ማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ በመሆናቸው ዲጂታል እውቀት በመጨመር ቴክኖሎጂን ለጤና፣ለንግድ እና ለመልካም ነገር እንዲያውሉት ጠይቀዋል።

በዚህ ረገድ መንግሥት ዲጂታል ኢኮኖሚን በመገንባትና የግሉን ዘርፍ የማበረታታት ሥራዎች እየሠራ ነው። ዘርፉ በርካታ የሥራ ዕድሎች የሚፈጠርበት መሆኑ ልዩ እንደሚያደርገው ገልጸው፤ ተወዳዳሪ ለመሆን፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ጥራት ያላቸውን ምርቶች ለማምረት፣ ሀብትና ጊዜን ለመቆጠብ እና ለመሳሰሉት ሁሉ ቴክኖሎጂን መጠቀም የግድ በሚል ወቅት ላይ እንገኛለን ብለዋል።

ለቴክኖሎጂ ቅርብ የሆነውን ወጣት የዲጂታል እውቀት እንዲኖረው ለማድረግ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ በኃይሉ፤ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025ን በተለያዩ አካባቢዎች እያስተዋወቀ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በስልጠናው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የፈጠራና ባህል ልማት ኃላፊ አቶ ካሳሁን ኤሊያስ፤ ወጣቶች የማህበረሰቡን ችግር በመለየት የፈጠራ ሥራዎችን እውን ማድረግ የሚችሉባቸውን መንገዶች በስልጠናው አሳይተዋል። በስልጠናው ወጣቶች የስታርት አፕ የፈጠራ ሃሳቦችን እንዴት ማበልጸግ እንደሚችሉ ገለጻ ተደርጎላቸዋል።

የስልጠናው ተሳታፊ ወጣት መስከረም ግዛው በሰጠችው አስተያየት፤ ስልጠናው የወጣቱን አዕምሮ የሚያንጽና ለፈጠራ ሥራዎች እንዲነሳሳ የሚያደርግ ነው። "ከስልጠናው ያገኘሁትን ፍሬ ሃሳብ በአካባቢዬ ለሚገኙ ወጣቶች በማካፈል ወጣቶች ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ብላለች።

ሌላኛው የስልጠናው ተካፋይ ወጣት ማሞ አለማየሁ በበኩሉ፤ ስልጠናው ወጣቶች በዲጂታል ቴክኖሎጂ ዙሪያ ምን አይነት እውቀትና ግንዛቤ ሊኖራቸው እንደሚገባ ያስተምራል። ስልጠናው ለወጣቶች የሚሰጠው ጥቅም ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብሏል።

በተመሳሳይ ኢፕድ በስልጠና ማዕከሉ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች በሦስት ርዕሰ ጉዳዮች ሥልጠና እየሰጠ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡ እነዚህም በማህበራዊ ሚዲያ ማኔጅመንት፣ በኦዲዮ ቪዥዋል ማኔጅመንትና በዲጂታል ማርኬቲንግ ማኔጅመንት ላይ ያተኮረ ነው።

በስልጠናው 70 የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች የሚሰለጥኑ ሲሆን፤ በትናንትናው እለት 30 ሰልጣኞች በማህበራዊ ሚዲያ ማኔጅመንት ዙሪያ መሰልጠን ጀምረዋል። የተቀሩት ሰልጣኞች በቀጣይ በኦዲዮ ቪዥዋል ማኔጅመንት እና በዲጂታል ማርኬቲንግ ማኔጅመንት ላይ የሚሰለጥኑ እንደሚሆን ተገልጿል።



አቶ ሽመልስ ታምራት

# ኮርፖሬሽኑ በሥነምግባርና በሙስና መከላከል ላይ ያተኮረ የለውጥ ሥራ እያከናወነ መሆኑን አስታወቀ

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በሥነምግባርና መጎልበትና በሙስና መከላከል ላይ ያተኮረ የለውጥ ሥራ እያከናወነ መሆኑን የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

ኮርፖሬሽኑ "በሥነምግባር የታነፀ አመራርና ባለሙያ በመገንባት ከሙስና የፀዳ ተቋም እንፍጠር" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት ስልጠና ሰጥቷል፡፡

በወቅቱ የኮርፖሬሽኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት እንደገለጹት፤ የኮርፖሬሽኑ ክፍተት በዋናነት የሥነ-ምግባር ጉዳይ በመሆኑ የተቋሙን አሠራር የመፈተሽ ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

ችግሩን ለመቅረፍ ተቋሙ የአሠራር ለውጦችን እያደረገ መሆኑን አንስተው፤ የሥነ-ምግባር ጉዳይ ተቋሙን ለመለወጥ ወሳኙ ጉዳይ በመሆኑ ለውጡን ከሙስና ትግሉ ጋር በማስተሳሰር እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፣ በተቋሙ ግልጸኝነት እንዲኖር ከወረቀት የጸዳ አሠራር ለመዘርጋት እየተሠራ ነው፡፡ ተቋሙ ከእጅ ንክኪ የሆኑ አሠራሮችን ለመተግበርና አሠራሩን ለማዘመን የሚረዱ በቅርብ ጊዜያት ስድስት ሶፍትዌሮችን አበልጽጓል፡፡

ከዚህ በፊት 10 የነበሩት የተቋሙ ቅርንጫፎች ወደ አራት እንዲጠቃለሉ መደረጉን አስታውቀው፤ ተቋማቱ ወደ አራት ዝቅ እንዲሉ መደረጉ ጠንካራና ለቁጥጥር የሚያመቹ እንዲሆን ያግዛል ሲሉ አስረድተዋል።

ተቋሙ በርካታ ሀብቶችን የሚያንቀሳቅስ እንደመሆኑ በከተማዋ ለሙስና ተጋላጭ ተብለው ከተቀመጡ መሥሪያ ቤቶች አንዱ ነው ያሉት አቶ ሽመልስ፤ ችግሩን ለመቅረፍ የለውጥ ሥራ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት በየክፍሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩን ተናግረዋል።

ወደ ለውጥ ተግባሩ በስፋት ከመግባታችን ቀደም ብሎ፤ ሙስናን የሚጸየፍ አመራር ማፍራት ወሳኝ ነው ያሉት አቶ ሽመልስ፤ የስልጠናው ዓላማ ሪፎርሙን ማሳካት የሚችል በሥነምግባር የበቃ አመራር ማፍራት ነው ብለዋል።

ስልጠናውን ሲከታተሉ የነበሩት በተቋሙ የፕላንና ዲዛይን ዳይሬክተር አቶ ፍቃዱ ዓለሙ በበኩላቸው፤ በሥነ-ምግባር ላይ የተሰጠው ስልጠና የተጀመረውን የለውጥ አሠራር ወደ መሬት ለማውረድ እድል የሚፈጥር ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የቤቶች ልማት ዘርፉ ለሙስና ተጋላጭ ነው ፤ ስለዚህ በሥነ-ምግባር የታነጸና ከብልሹ አሠራር የጸዳ ሥራ ለማከናወን ተመሳሳይ ስልጠናዎች አስፈላጊ መሆናቸውን አንስተዋል።

በኮርፖሬሽኑ የውለታ አስተዳደርና የገበያ ጥናት ቡድን መሪ አቶ ዳዊት ዘውዴ በበኩላቸው፤ ለውጡን ተከትሎ የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች በአዳዲስ የሥራ መደቦች መመደባቸውን አስረድተዋል።

ስለዚህ አመራሩና ፈጻሚው አካል ሥነምግባርን ተላብሶ በይበልጥ መሥራት እንዲችል የተሰጠው ስልጠና አስፈላጊ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# የምርምርና የጥናት ሥራዎች ወደ ተግባር የሚቀየሩበት አቅጣጫ ተቀምጧል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሠሩ አብዛኛው የምርምርና የጥናት ሥራዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተው እየተሠራ መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ኮራ ጡሽኔ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የምርምር ሥራዎች ወደ ተግባር ተቀይረው ችግር ፈቺ እንዲሆኑ የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተው እየተሠራ ነው፡፡

ሚኒስቴሩ ዩኒቨርሲቲዎች ጥራቱን የጠበቀና ትክክለኛ የምርምር ሥራዎች እንዲሠሩ ለማድረግ ከሚያከናውናቸው የድጋፍና ክትትል ሥራዎች ጎን ለጎን የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች፣ የሚሠሩ ምርምሮች በኩረጃ ተደጋጋሚ እንዳይሆኑ የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በማቅረብ ችግሩ እንዲፈታ እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

አቶ ኮራ፤ ጥልቀት ያላቸው የምርምር ሃሳቦች የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ከመምህራኖቻቸው ጋር በጋራ መሥራት የሚችሉበት፣ ቁልፍ የምርምር ፍላጎቶች ላይ ያተኮሩ አጀንዳዎች እንዲሠሩ እንዲሁም ተመራማሪዎች በተናጠል ከሚያደርጉት አሠራር በመውጣት በጋራ እንዲሠሩ ለማስቻል የፖሊሲና የአፈጻጸም ስልትና መመሪያ ተቀርጾ ወደ ሥራ ገብቷል ብለዋል፡፡

በቀጣይም የምርምር ሥራዎች የበለጠ የሕዝቡን ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ለማስቻል በየዩኒቨርሲቲዎች የሚሠሩ የጥናት ሥራዎች ድግግሞሽ ለማስቀረት የትኩረት አቅጣጫ እንዲኖራቸው የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት አቶ ኮራ፤ የምርምር መሠረተ ልማቶች ማሟላት፣ የሰው ኃይል ልማት ማሳደግና በተቋማቱ አስተማማኝ ቴክኖሎጂ እንዲኖር ትኩረት መደረጉን አብራርተዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲዎች በርካታ የምርምርና የጥናት ሥራዎች ቢሠሩም አብዛኞቹ ተግባር ላይ እንደማይውሉ በመጥቀስ፤ ዩኒቨርሲቲዎቹ ልምድ ካላቸው የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር እንዲሠሩ እየተደረገ እንደሚገኝ አመልክተዋል፡፡

እንደ አቶ ኮራ ገለጻ፤ የሚታተሙ ጥናቶች ለፖሊሲ ግብዓት የሚውሉና ለውሳኔ ሰጪዎች የሚያገለግሉ ከማድረግ አኳያ ጥሩ ጅምር ቢኖርም ከሚፈለገው አንጻር ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህንንም ውስንነት ለመቅረፍ የምርምር ውጤቶች ወደ ማበልጸጊያ ማዕከላት ገብተው ወደ ተጨባጭ ውጤት እንዲቀየሩ እየተደረገ ይገኛል፡፡

አቶ ኮራ፤ የሚሠሩ ምርምሮች ዓላማቸው ከመመረቂያነት ያላለፈ መሆን፣ የጥራት ማነስ፣ የምርምር አጀንዳ መዛባት፣ ምርምሮችን በቅንጅት አለመሥራት፣ የበጀት እጥረት፣ የተቋማት የታተሙ የምርምር ውጤቶች የመጠቀም ልምድ አለማደግ እንዲሁም የምርምር ውጤቶች የስርጭት ውስንነትና የማስተዋወቅ ሥራ አብዛኛውን ወደ ተግባር እንዳይቀየሩ ካደረጉ ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡



አቶ ኮራ ጡሽኔ

በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ለምርምር ቢወጣም የሀብት ውስንነት አለ ያሉት አቶ ኮራ፤ መንግሥት ከሚመድበው ሀብት በተጨማሪ የምርምር ተቋማት ፈንድ የሚያገኙበትንና የተመደበላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ አሟጠው እንዲጠቀሙ የሚያደርጉ አሠራሮች እንደሚዘረጉ ጠቁመዋል፡፡

ዜና

# ከሀገር ውስጥ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ማጠናከር እንደሚገባ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰቧል።

ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሦስተኛ ዓመት 28ኛ መደበኛ ስብሰባው የቱሪዝም ሚኒስቴርን የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸምን ገምግሟል።

የተቋማቸውን ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡት የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ፤ ወደተለያዩ አካባቢዎች ከተንቀሳቀሱ 30 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች 48 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር መገኘቱንም ገልጸዋል።

በቱሪዝም ዘርፉ ለ81 ሺህ 673 የሥራ ዕድሎች መፈጠሩን ጠቁመው፤ በሀገር ውስጥ 19 ዓለም አቀፍ ሁነቶች ማካሄድ መቻሉን፣ በማህበራዊ ሚዲያና የበይነ መረብ አማራጮችን በመጠቀምም የቱሪስት መስህቦችን የማስተዋወቅና መረጃ የማሰራጨት ሥራ መከናወኑንም አስረድተዋል።

የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን በማጎልበት ዘርፉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ በማሳደግ በኩልም፤ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ባህል ማደግ መቻሉንም ጠቁመዋል።

የልወቅሽ ኢትዮጵያ ዘመቻ በማጠናከር የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ባህልን የሚደግፍ የባንክ ቁጠባ አሠራር እንዲዘረጋ ተደርጓል ብለዋል። ዘመናዊ የቱሪዝም ሳተላይት የመረጃ ሥርዓት እየተዘረጋ እንደሚገኝም አስታውቀዋል።

በኢኮ-ቱሪዝም፣ በግብርና፣ በታዳሽ ኃይል አቅርቦት፣ በአነስተኛ ኢንተርፕራይዞችና በዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀሞች 29 ሺህ 300 የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ በማድረግ ከ52 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መገኘቱን አንስተዋል።

የውጭ ጎብኚዎች ፍሰትና የቱሪዝም ገቢን በማሳደግ በኩል በዘጠኝ ወራት 861 ሺህ 126 ቱሪስቶችን ወደ ሀገር እንዲገቡ በማድረግ ከዘርፉ ሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ማግኘት መቻሉን ገልጸዋል።

የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎች በተሠራው የሕግ ማስከበር ሥራም፤ በፓርኮች ላይ የደረሱ ጫናዎች በ66 በመቶ እንዲቀንሱ መደረጉን የተናገሩት አምባሳደር ናሲሴ፤ ዘርፉ አሁንም ዘርፉ የመንግሥትን ትኩረት እንደሚሻ አመልክተዋል።

በባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክና በሰንቀሌ ቆርኪዎች መጠለያ ውስጥ በሕገ ወጥ መንገድ የተገነቡ 490 ቤቶች እንዲፈርሱ መደረጉን፣ በባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ውስጥ የተሰጠው 200 ሄክታር ያልተጣጣመ የእርሻ ኢንቨስትመንት እንዲቆም መደረጉንና በአልጣሽ ብሔራዊ ፓርክ ሁለት ሺህ 400 ሄክታር ቦታ ከልቅ ግጦሽ ነጻ መደረጉን በአብነት ጠቅሰዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በበኩሉ፤ የቱሪዝም ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚጠበቅበትን ድርሻ እንዲያበረክት አስቻይ ሁኔታ መፍጠር፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሳተፉ ማድረግ እንደሚገባ አሳስቧል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ወይዘሮ አይሻ ያህያ፤ ሚኒስቴሩ ያላከናወናቸውና አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተግባራት ላይ በቀሪ ጊዜ ርብርብ በማድረግ ማከናወን እንዳለበት ተናግረዋል። የቱሪስት መዳረሻና መስህቦችን ማስፋት፣ በነባሮች እሴት የመጨመር ሥራ አሁንም ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አመላክተዋል።

የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች የመጎብኘት ባህል እንዲያድግ በትኩረት እንዲሠራ፣ ተገልጋይ ተኮር አገልግሎት እንዲሰጥ ባለሙያዎችን ማብቃት እንደሚገባም ተናግረዋል።

በቀረበው ሪፖርት መነሻነት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የምክር ቤት አባላትና ለሕዝብ ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ ሀገር ውስጥ ያለው የሰላም ችግር ዘርፉ ላይ ጥላ ማጥላቱን ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ አስረድተዋል።

አምባሳደር ናሲሴ ዘርፉን ለማሳደግ በመንግሥትና በግል ሽርክና በቅንጅት የሚሠሩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች መኖራቸውን አመላክተዋል። የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ አስቻይ ያልነበሩ ሕጎችን የማሻሻል ሥራዎች መከናወናቸውንም ጠቁመዋል።

መሬት ከማቅረብ አንስቶ ለግሉ ዘርፍ ድጋፍ ይደረጋል፣ ለኢንቨስትመንቱ የሚያገለግሉ ዘመናዊ ተሽከርካሪዎች፣ የግንባታ እና የቁሳቁስ እቃዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ ተፈቅዷል ብለዋል።

የጎብኚዎችን የቆይታ ጊዜና የቱሪስት ፍሰትን ለማሳደግ፣ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለማድረግም በተመረጡ መዳረሻ ስፍራዎች ሄሊኮፕተር በቀላሉ እንዲያርፍባቸው ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝም አንስተዋል። ሚኒስትሯ ቅርስ ማስመዝገብን በተመለከተ በብሔራዊ ደረጃ የሚመራ ኮሚቴ መቋቋሙን አስታውቀዋል።

# ኢትዮጵያ የቻይና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሀብታዊ ልማት መሥራት ይገባል ሲሉ አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ በቻይና-አፍሪካ ትብብር ፎረም ተሳትፎዋ ከቻይና ጋር ያላትን ትብብር ብቻ ሳይሆን ቻይና ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያላትን የልማት ትብብር እንዲጠናከር ትልቅ ሚና መጫወቷን አንስተዋል።

በቀጣይም በቻይና-አፍሪካ ትብብር ፎረም በንቃት በመሳተፍ በኢትዮጵያና ቻይና እንዲሁም እንደአጠቃላዩ በቻይናና በአፍሪካ መካከል ያለው የልማት፣ የንግድ፣ የኢንቨስትመንትና ሌሎች ትብብሮች የበለጠ እንዲጠናከሩ የበኩሏን ሚና ትወጣለች ብለዋል።

በኢትዮጵያ የቻይና ኤምባሲ አማካሪ ሚኒስትር ያንግ ይሀንግ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የቻይና-አፍሪካ ትብብር ፎረም ከአፍሪካ ጋር በተግባር የተደገፉ በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑበት መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በቻይና እና አፍሪካ መካከል ያለው ኢኮኖሚያዊ ትብብር እንዲጎለብት የመሪነት ሚናዋን እንደምትጫወት ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ያንግ ይሀንግ ገለጻ፤ በርካታ የቻይና ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ኢንቨስት እያደረጉ ነው። የቻይና አፍሪካ ትብብር ፎረም በመመስረቱም ግንኙነታቸው ዘርፈ ብዙ እንዲሆን አስችሏል።

እንዲሁም በኢትዮጵያና በቻይና መካከል ያለው ኢኮኖሚያዊ ትብብር በየዓመቱ እያደገ መሆኑን አማካሪው አንስተው፤ ኢትዮጵያም የግብርና ውጤቶችን ወደ ቻይና ገበያ በስፋት እየላከች መሆኑን አስታውቀዋል።

ይህንን የትብብር ማዕቀፍ መሠረት በማድረግ ቻይና ኢትዮጵያን ጨምሮ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ጋር በበርካታ የልማት ዘርፎች ላይ በጋራ እየሠራች እንደምትገኝም አስረድተዋል።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከፍተኛ ተመራማሪና የእስያ ፓሲፊክ ዳይሬክተር ጄኔራል አንተነህ ጌታቸው (ዶ/ር)፤ ጉባኤው ያተኮረው በትብብር ፎረሙ ላይ እያጋጠሙ ባሉ ተግዳሮቶችና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በቻይና-አፍሪካ መካከል ያለው የልማት ትብብር እንዲጠናከር የወካይነት ሚናዋን አጠናክራ እንደምትቀጥል ገልጸዋል።

በቻይና-አፍሪካ ትብብር ፎረም ሂደት ውስጥ ኢትዮጵያ ቁልፍ ተሳትፎ እያደረገች መሆኑን ያነሱት ዶክተር አንተነህ፤ ጉባኤው በርካታ የልምድ ልውውጦች ለማድረግ ዕድል የሚፈጥርና ትብብሩን ይበልጥ ለማጠናከር ያሉ ዕድሎችን ለመጠቀም እንደሚያስችል አመላክተዋል።

እንደ ዶክተር አንተነህ ከሆነ፤ የቻይና አፍሪካ ትብብር ፎረም የልማት ትብብሩን ለማጠናከር በማለም እ.አ.አ. በ2000 የተቋቋመ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ላለፉት 24 ዓመታት አባል ነች።

ጉባኤውን የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩትና በኢትዮጵያ የቻይና ኤምባሲ በጋራ ያዘጋጁት ሲሆን፤ በውጭ ግንኙነት ዘርፍ ከፍተኛ ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ተሳትፈውበታል።

# 12ነጥብ1ሚሊዮን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የክልሎች የጋራ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማና የቀጣይ ተግባራት ዕቅድ ላይ ትናንት ውይይት አድርጓል።

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ(ዶ/ር)፤ በዘንድሮ ዓመት 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ መገዛቱን ተናግረው፤ እስከ አሁንም 12 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ተጓጉዟል ብለዋል።

ይሄ በኢትዮጵያ የማዳበሪያ ግዢ ታሪክ ትልቅ ቁጥር መሆኑን ገልጸው፤ የገባውን የማሰራጨት እና ለአርሶ አደሩ የማድረስ ሥራ ክልሎች በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ ተናግረዋል። የማዳበሪያ ግዢው በወቅቱ በመፈጸሙ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ባነሰ ገንዘብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ብልጫ ያለው ማዳበሪያ መገዛቱን ጠቁመዋል።

በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በዘንድሮ ዓመት ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኝ ይዘጋጃል ተብሎ መታቀዱን ያስታወሱት ግርማ(ዶ/ር)፤ አሁን ላይ 7 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል። ችግኞቹ 650ሺ ሄክታር ላይ ካርታ ወጥቶላቸው እንደሚተከሉ ጠቁመዋል። እስከአሁንም ስድስት መቶ ሺ ሄክታር መሬት ካርታ መለየቱን ገልጸዋል። በአጠቃላይ የችግኝ ቁጥር በሄክታር ሲሰላ ዘንድሮ ተከላ የሚደረግበት አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንደሚሆንም ጠቅሰዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ካርታ በወጣላቸው ቦታዎች ላይ በተከላው እለት የሚተክለው ሕዝብ ብዛት እና በሚተከለው ችግኝ መጠን እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች ላይ በዩኔስኮ ለማስመዝገብ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

በምርት ዘመኑ በመስኖ ልማት 120 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ እስከ አሁን 90 ሚሊዮን ኩንታል በመሰብሰብ የእቅዱን 99 በመቶ ማሳካት መቻሉን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ጭማሪ እንዳለው አመላክተዋል።

ዘንድሮ በበልግ እርሻ ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰብል መሸፈን ተችሏል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በሌማት ትሩፋት ሥራዎችም በግብዓት አቅርቦት እና በምርት ከእቅድ በላይ አፈጻጸም መመዝገቡን ተናግረዋል።

በዓመቱ በሁሉም ዘርፎች አበረታች ውጤቶች መመዝገባቸውን የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ በተፈጥሮ ሀብት በተፋሰስ ሥራዎች ሕዝቡን በማስተባበር በተሠራው ሥራ የሚጨፈጨፉ ደኖችን በእጅጉ መቀነስ ተችሏል ብለዋል።

ከስድስት ሺ በላይ እስከአሁን ድረስ ያልነበሩ ተፋሰሶች የአስተዳደርና የአጠቃቀም እቅድ ተዘጋጅቶላቸው እንዲተዳደሩ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ በተፋሰስ ሥራ ኢትዮጵያ ያላትን ተሞክሮ ለአፍሪካ ሀገራት ማካፈል መቻሉን አመልክተዋል። ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚኒስቴሩ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ መሆኑንና የዘንድሮ ክረምት ለግብርናው ዘርፍ የተሻለ መሆኑን ጠቁመዋል።

# ለቱሪዝም ምቹ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መንግሥት በተጠኑ ጥናቶች አማካኝነት መለየቱን ያስታውሳሉ።

ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው አብዛኛው ቱሪስት ካደጉት ሀገራት ነው። እነዚህን አስደስቶ ለመሸኘት ከፍተኛ ፕሮቶኮልና ጽዳት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ማቆየት ይጠበቃል። የጽዱ ኢትዮጵያም ንቅናቄ ጎብኚዎች ረዘም ያለ ጊዜ እንዲያሳልፉ ለማድረግና እነሱን እንደማስታወቂያ በመጠቀም ሌሎችን ለመሳብ ያስችላል ይላሉ።

ቱሪስቶች ንጹህ ነገር ማግኘት ያለባቸው ደግሞ በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች አካባቢና በሚስተናገዱባቸው ሆቴሎች ብቻ ሳይሆን በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎችና ከተሞች ሁሉ ሊሆን ይገባል የሚሉት ተመራማሪው፤ ከአየር ማረፊያ ጀምሮ ሲንቀሳቀሱ የሚያዩትና የሚጓዙበት መንገድ ሁሉ ስለኢትዮጵያ በቀድሚያ የሚነገራቸው ነገር አለ ሲሉ ያስረዳሉ።

እንደ ኬንያ ያሉ ሀገራት በዘርፉ በቅኝ ግዛት ዘመናቸው በእንግሊዞች የተጀመሩ ስራዎች ስላሉ ከእኛ በብዙ መልኩ በተሻለ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ነው የሚጠቁሙት። ይሄ ማለት ግን እኛም ከቅኝ ግዛት ብቻ መማር አለብን ማለት አይደለም። ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት የምትሻለው በአሏትና ወደፊት በሚለሙት የቱሪዝም ሀብቶቿ ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተሠሩ ሥራዎች ጥቂት የተመዘገቡ ለውጦች ቢኖሩም ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በዚህ ረገድ ብዙ ሥራ የሚጠብቃት በመሆኗ የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት ግን እንደ ማህበረሰብ ንቃተ ህሊና ማዳበር ላይ መሥራት ይጠበቃል ይላሉ።

ለአብነት በእስራኤል ሀገር እያንዳንዱ ዜጋ ለከተማው ውበት አብዝቶ ይጨነቃል። አንዳንድ ጊዜ ከእጃቸው ያለውን ቆሻሻ ለማስወገድ ረጅም መንገድ ይጓዛሉ እንጂ በፍጹም መሬት ላይ አይጥሉም። በመሆኑም ከመሠረተ ልማት ማስፋፋት በተጓዳኝ የማህበረሰብ ንቃተ ህሊና እንዲለወጥ ማድረግም የሚጠበቅ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

« ሁሉም ከተሞች የየራሳቸው መገለጫና መለያ ሊኖራቸው ይችላል። በጽዳት ጉዳይ ግን የተሻለ ሆኖ መገኘት የግድ ነው» ያሉት ደግሞ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝምና ሆቴል ማኔጅመንት መምህሩ ውብሸት ካሳ ናቸው።

እንደ ሩዋንዳ፣ ደቡብ አፍሪካና ሲሼልስ ያሉ ሀገራት ከፍተኛ የጽዳት አጠባበቅ ስላላቸው ለቱሪስት ተመራጭ ሀገራት ናቸው። ኢትዮጵያ ግን በዚህ ረገድ ጥያቄ ውስጥ ናት ይላሉ።

እንደ መምህር ውብሸት ማብራሪያ፤ ሁሉም ጎብኚዎች ሊባል በሚችል ደረጃ ከሀገራቸው ሲነሱ ከተለያየ ወገን መረጃ ይሰበስባሉ። ይህንንም መነሻ በማድረግ የሚጠብቁት ነገር ያለ ሲሆን፤ ወደ አፍሪካ ሲመጣ ጽዳትን ጨምሮ ብዙ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮች ይገጥሙናል ብለው ያስባሉ።

በቆይታቸውም የከተማ የቱሪስት መዳረሻዎችን ሊያዩ ወይንም ወደ መዳረሻዎች ሲሄዱ በሚያርፉባቸው ከተሞች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የእግር ጉዞ ማድረጋቸው አይቀርም። በዚህ ጊዜ ጽዱ ነገሮችን እንዲመለከቱ ማድረግ ይጠበቃል። በመሆኑም መንግሥት በዘመቻ መልክ የጀመረው የከተሞች ጽዳት ከታለመለት ዓላማ ባሻገር ለቱሪዝምና ለሀገር መልካም ገጽታ ግንባታ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ያመላክታሉ።

በማንኛውም ሁኔታ ወደ አንድ ከተማ የገቡ ሰዎች የቆይታ ሁኔታ የሚወሰነው ከሰላምና ከኑሮ ውድነት ቀጥሎ ጽዳት ላይ በሚኖረው ሁኔታ ነው ያሉት መምህሩ፤ የሁነት ቱሪዝም ማለትም ስብሰባ፤ ኤግዚቢሽንና የጎዳና ላይ በዓላትን ጨምሮ ሌሎችም በርካታ ታዳሚ ለሚስተናገድባቸው ሁነቶች ጽዳት ወሳኝ መሆኑን ያስረዳሉ።

ለዚህ ደግሞ በሆቴሎችና አዳራሾች የሚኖሩት የንጽህና መጠበቂያዎች በቂ አይሆኑም። በመሆኑም የግድ ደረጃቸውን የጠበቁ የሕዝብ መገልገያዎች ያስፈልጋሉ ሲሉ ይገልጻሉ።

ሰዎች በአንድ ከተማ የሚኖራቸው ቆይታ በጨመረ ቁጥር ደግሞ ለከተማዋ የገቢ ምንጭ መሆናቸው አይቀርም፤ ይህም በከተሞች ረገድ በዚህ ረገድ ጤናማ ፉክክር በመፍጠር የቱሪዝም እድገት እንዲኖር ይረዳል ይላሉ።

ከዚህ ቀደም በከተሞችና በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች የጽዳት ሳምንት እየተባለ የተጀመሩ በርካታ ሥራዎች ቢኖሩም ከአንድ ወቅት የዘለሉ አልነበሩም። የተጀመረው ሥራ ብልጭ ድርግም የሚል ከሆነ የሚፈጥረው ተጽእኖ ስለሚኖር ለቀጣይነቱ ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ይጠቁማሉ። የከተሞች ጽዳት ጅማሮ ተነሳሽነት በመንግሥት መሆኑ ተገቢና ይበል የሚያሰኝ ነው። ነገረ ግን ከጉዳቱም ከጥቅሙም ሁሉም ማህበረሰብ ተቋዳሽ እንደመሆኑ በከፍተኛ ትኩረት ሊሳተፍበት ይገባል ሲሉ ምክረ ሃሳብ ሰንዝረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የተመዘገበው የማክሮ ኢኮኖሚ ዕድገት የሀገር በቀል ኢኮኖሚው ስኬት ማሳያ ነው !

በተያዘው የ2016 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ7 ነጥብ 9 በመቶ እንደሚያድግ ከኢትዮጵያ መንግሥት በተጨማሪ የዓለም ገንዘብ ድርጅትን ጨምሮ ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማትም የተጋሩት ትንበያ ነው፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ወራትም ይኸው ትንበያ ሊሳካ እንደሚችል የሚያሳዩ በርካታ የማክሮ ኢኮኖሚ አመላካች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

ግብርና አንዱ የማክሮ ኢኮኖሚ ዕድገቱ ማሳያ ነው፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ወራትም በግብርና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ የታየ ሲሆን፤ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በዋናዋና ሰብሎች ላይ የ100 ሚሊዮን ኩንታል ጭማሪ ታይቷል፡፡ በበጋ ስንዴ ልማትም አይነተኛ ለውጥ የታየ ሲሆን፤ አምና በዘጠኝ ወራት ከነበረው የ47 ሚሊዮን ኩንታል ምርት በዘንድሮው ዓመት ወደ 80 ሚሊዮን ኩንታል ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይም የሩዝ ምርትን አምና በዘጠኝ ወር ውስጥ ከነበረው የ8 ሚሊዮን ኩንታል ባለፉት ዘጠኝ ወራት ወደ 38 ሚሊዮን ኩንታል ማሳደግ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ከአምናው አንጻር ወተት በሁለት ቢሊዮን ሊትር፣ እንቁላል በአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን፣ ስጋ በ200 ሺህ ቶን ብልጫ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ የግብርናው ዘርፍ ያሳየው እምርታ ኢትዮጵያ በ2016 በጀት ዓመት ያስቀመጠችውን 7 ነጥብ 9 በመቶ ዕድገት ለማሳካት አቅም እንዳላትና የተቀየሰውም ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲም ፍሬ እያፈራ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ በኢንዱስትሪ ዘርፉም የማምረት አቅም፣ የግብዓት አቅርቦት፣ የኢነርጂ አጠቃቀም እና የብድር አቅርቦቱ መሻሻል አሳይቷል፡፡

በአገልግሎት ዘርፉም መሻሻሎች የታዩ ሲሆን፤ በተለይም ኢትዮጵያ አየር መንገድ 25 በመቶ በገቢና ተያያዥ ዘርፎች እምርታ አሳይቷል፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ካጓጓዛቸው መንገደኞችና ዕቃዎች 5ነጥብ 8ቢሊዮን ዶላር ተገኝቷል፡፡ወደ ውጭ ከተላኩ ሸቀጦችም 2ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ማግኘት የታቻለ ሲሆን፤ በበርካታ ችግሮች ተተብትቦ የነበረው የማዕድን ዘርፉም መሻሻሎችን አሳይቷል፡፡ከወርቅ ንግድ ብቻ 275 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል፡፡ ከቅባት እህሎችም 264 ሚሊዮን ዶላር ገቢም ተመዝግቧል፡፡ከውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትም የተገኘው ገቢ 2ነጥብ 8 ቢሊዮን ደርሷል፡፡

ሆኖም ኢኮኖሚው ተስፋ ሰጪ ውጤቶች የተገኙበት ቢሆንም ከሥራ ዕድል ፈጠራ፤ ከዋጋ ግሽበትና ከውጭ ዕዳ ተጋላጭነት አንጻር አሁንም ያልተቀረፉ ተግዳሮቶች አሉ፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለ2 ነጥብ 1 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ቢቻልም አሁንም ካለው ሰፊ የሥራ ፍላጎት አንጻር ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ግድ ይላል፡፡

በሌላ በኩል የዋጋ ግሽበት አሁንም ትልቁ የሀገሪቱ ፈተና ነው፡፡ አሁን ያለው የዋጋ ንረት አምናና ካቻምና ከነበረበት የ33 በመቶ ደረጃ ወደ 23 ነጥብ 3 በመቶ ዝቅ ቢልም አሁንም የኑሮ ውድነቱን በማባባስ ረገድ ፈተና ሆኖ ዘልቋል፡፡ በተለይም የምግብ ዋጋ ንረት 27 በመቶ መሆኑ ችግሩ ዝቅተኛውን የኅብረተሰብ ክፍል የሚጎዳ ነው፡፡

ይህንን ችግር ለመቀነስ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ጥረት መደረጉ ፤የገንዘብ ዝውውሩን ለመቀነስ የገንዘብ እና ፊሲካል ፖሊሲ በጥብቅ መተግበሩና ነዳጅን በመሳሰሉ ቀጥተኛ የኑሮ ውድነትን በሚያስከትሉ ሸቀጦች ላይ ድጎማ መደረጉ የኑሮ ውድነቱ አሁን ካለበት እንዳይጨምር አስተዋጽኦ ያደረጉ ቢሆንም ካለው የኅብረተሰባችን የመግዛት አቅም አንጻር በቀጣይ በርካታ ጥረቶችን በማድረግ የዋጋ ግሽበቱ ከተቻለ እንዲቀንስ ካልሆነ ባለበት እንዲቆም ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ ያለባት የውጭ ዕዳ ተጋላጭነት አሁንም ፈተና ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በተለይም ባለፉት መንግሥታት ጭምር የተወሰዱ እዳዎችን መንግሥት የመክፈል ግዴታ የወደቀበት በመሆኑ ለመደበኛ እና ለካፒታል ዘርፎች ከሚያወጣው ወጪ በተጨማሪ በየዓመቱ ለውጭ አበዳሪ ሀገራትና ተቋማት የሚከፍለው ዕዳ ከፍተኛ ነው፡፡ መንግሥት ባለፉት አምስት ዓመታትም ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ በመክፈል የሀገሪቱን የዕዳ መጠን ለመቀነስ ችሏል፡፡

በአጠቃላይ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ መተግበር ከጀመረ ወዲህ ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች እያስመዘገበችው ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት አበረታች ነው፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የተመዘገበው ውጤትም የሚያሳየው ይህንኑ በመሆኑ በተለይም በ2016 በጀት ዓመት የተቀመጠውን የ7ነጥብ9 በመቶ ዕድገት ትንበያ ሙሉለሙሉ ለማሳካት የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ጽዱ ኢትዮጵያ - ለአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ

አዲስ መንገድ

በዓለማችን ንፁህና ፅዱ ከሆኑ ሀገራት መካከል ጃፓን በቀዳሚነት ትጠቀሳለች። ይህቺ የሩቅ ምሥራቅ ፈርጥ ከተሞቿን፣ የተፈጥሮና የመስህብ ስፍራዎቿን ማፅዳት እንደ ሥራ ሳይሆን ልክ እንደ ባህል አድርጋ ይዛዋለች፤ ጽዱነት በእጅጉ ተዋህዷታል፡፡

ጃፓናዊያን አንድ በፍፁም የማይታሙበት ጉዳይ የቤትና የአካባቢያቸውን ፅዳት መጠበቅ ላይ ነው። ይህ ባህላቸው ታዲያ ዛሬም ለእኛ ምሳሌ ሆኖ ጥንካሬያቸውን እንድናወራላቸው አስገድዶናል። በተለይ ዛሬ ለምናነሳው የሀገራችን የንጽህና እና የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ ጃፓናዊያን ጥሩ ምሳሌ ናቸውና ጥቂት ተጨማሪ ሃሳቦችን ስለዚህች ሀገር የጽዳት ጉዳይ እናነሳና ወደ ዋናው ሀገራዊ ጉዳያችን እንሸጋገራለን።

በጃፓን ስፖርት ዝግጅቶች ምክንያት እዚህም እዚያም ቆሻሻን ማንሳት ግዴታ ሳይሆን ባህል ነው። ይህንን ከፍተኛ የንጽህና ደረጃ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ጭምር ደጋፊ ሆነው የሄዱ ጃፓናዊያን ሲተገብሩት ይስተዋላሉ። በሀገሪቱ ትምህርት ቤቶች የቡድን ፅዳት ሥራ ሁሌም ተግባራዊ ይደረጋል።

ተማሪዎች የህይወት ክህሎቶችን ለመማር ክፍሎቻቸውን ያፀዳሉ፤ የበጎ ፈቃደኞች የጽዳት ዝግጅቶች በየጊዜው ይካሄዳሉ፤ ዝግጅቶቹ ከስነምግባርና ከባህሪ ጋር የተቆራኙ ናቸው። በጎዳናዎች ላይ ምንም አይነት ቆሻሻ አይጣልም፤ በጎዳና ዳርቻና ጥጋ ጥጉ ላይ መፀዳዳት ብሎ ነገር የለም።

በጃፓን ንጽህናን መጠበቅ ለጤናና ውበት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ አዘውትሮ ማጽዳት የባክቴሪያ እና የበሽታ ስርጭትን ለመከላከል እንደሚረዳ ጃፓናዊያን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ይህ ባህላቸው ታዲያ በቱሪዝም ዘርፍ በዓለም አቀፍ ጎብኚዎች ተመራጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ የጃፓን ገፅታም በሚያስገርም ሁኔታ አዎንታዊ በሆነ መልኩ እንዲያድግ አስችሎታል። ለመሆኑ እኛ ኢትዮጵያውያን በዚህ ረገድ የቱ ጋ እንገኝ ይሆን?

ኢትዮጵያ የብዝሃነት መገለጫ ነች። በባህል፣ ታሪክ፣ ቅርስና ፈጥሮ ሀብት ከታደሉ ጥቂት ሀገራት መካከልም ትጠቀሳለች። ሕዝቧ የመከባበር፣ እንግዳን ከራስ በላይ አክብሮ የመቀበል፣ የመቻቻልና አብሮ የመኖር ጠንካራ ማህበራዊ መሠረት አለው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከጽዳትና አረንጓዴ ልማት አኳያ የሚከናወኑ ተግባሮች ቢኖሩም፣ ልክ እንደ ጃፓናዊያን እና ሌሎች በአካባቢ ጥበቃና ፅዳት ረገድ ስማቸው ከገነነ ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ ገና እጅግ ብዙ መስራት ይጠበቅብናል።

ከተሞቻችን ከውበትና ፅዳት አንጻር አንድ እርምጃ ወደፊት የተጠጉ አይደሉም። በዚህ ረገድ ደካማ ባህልና የትብብር ማነስ ይታይብናል፡፡ የቱሪዝም መስህብ የሆኑ መዳረሻዎቻችን ሳይቀሩ ትንሽ ሥራ በሚጠይቁ የፅዳት ጉድለቶች መስህብነታቸው ተሸፍኖ ይታያል፤ ለእዚህ ምክንያቱ ደግሞ በጽዳት በኩል ያለን ልማድና ትብብር ማነስ በምክንያት ሊጠቀስ ይችላል።

የቆሻሻ አወጋገዳችን እጅግ ደካማ የሚባል ለጤና እክልና ለአካባቢ ብክለት ጭምር የሚዳርግ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚካሄዱ ንቅናቄዎችና በጎ ጅምሮች እንዳሉ ሆነው፣ አሁንም በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ ያለን አፈፃፀም እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። አዲስ አበባ በሚል በአበባ የተሰየመ ከተማ ይዘን የሕዝብ መዳረሻዎቻችን ግን ለእይታም ለጤናም ምቹ ባልሆኑ የንፅህና ጉድለቶች ውስጥ ሆነው ይስተዋላሉ፡፡

ከዚህ አንፃር ለበርካታ ዓመታት የአፍሪካ መዲና የሆነችው፣ በተፈጥሮና በታሪኳ የብዙሃንን ቀልብ የምትስበው ኢትዮጵያ ከፅዳት አኳያ በሚታዩባት ጉድለቶች ገፅታዋ ተበላሽቶ ቆይቷል። ይህን ችግር የመፍታት ሥራ በመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶት ሲሠራበት ቢቆይም፤ ከችግሩ ስፋትና በጉዳዩ ላይ ዛሬም ካለው የአመለካከት ችግር ጋር በተያያዘ በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም በጽዳት በኩል ብዙ ርቀት መሄድ አልተቻለም፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ ተግባሮች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተወስደዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ግን ይህንን መጥፎ ገፅታ የሚቀይሩ በጎ ጅምሮችን እያስተዋልን ነው። በኢኮሚኖሚም በማህበራዊም ዘርፎች ሁለንተናዊ እድገት ለማስመዝገብ ከሚደረጉ ጥረቶች ጎን ለጎን በአካባቢ ጥበቃ እና ፅዱና ውብ ከተማን ለመገንባት ተግባራዊ የተደረጉ እርምጃዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው።

ውብ አሊያም ፅዱና ተፈጥሮው የተጠበቀ ሀገርና ከተሞች ለመገንባት ከምንም በላይ ትብብርና ቁርጠኝነት ያስፈልጋል። ከዚህ እሳቤ ጋር የተሳሰሩና የማህበረሰባችንን ግንዛቤ የሚቀርፁ ባህሎቻችንን አውጥተን ልንጠቀምባቸው ይገባል፤ ባህሎቻችን ይህን ለማድረግ የሚያነሱን ከሆነም ከውጪም ማምጣት ይቻላል፤ ብቻ ጽዱና ውብ እንሁን፡፡

በቅርቡ የተጀመረው የፅዱ ኢትዮጵያን መሰል ንቅናቄም በዘላቂነት የሚተገበርበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡ በዚህ ንቅናቄ ለመገንባት ለታሰቡ የመጸዳጃ ቤቶች ገቢ ለማሰባሰብ በተደረገ ጥረት ከእቅድ በላይ ሀብት ማግኘት ተችሏል፡፡ በዚያው ልክም ንቅናቄውን የሚደግፉ ሰዎችን ማፍራትም ተችሏል። ይህን ትልቅ አቅም ከፋይናንስ ድጋፉ በተጨማሪ ለማስተባበር ሥራም በሚገባ መጠቀም ይገባል፡፡

ከንቅናቄው እንደተገነዘብነው ፤ መንግሥት ከተሞችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ፣ ለኢትዮጵያ የሚመጥኑና ለዜጎች ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ የተቀናጀ የከተማ ልማት ፕሮግራም በመንደፍ ሰፋፊ ሥራዎችን በቁርጠኝነት እየሠራ ነው። የፌዴራል ተቋማት፣ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በከተሞች የሚካሄዱ ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሕዝብ ንቅናቄ የመፍጠር ዓላማ ያደረጉ ሥራዎች መጀመራቸው በቆሻሻ አወጋገድና በጽዳት አጠባበቅ ላይ ያለውን ስር የሰደደ ደካማ ልማድ ለመቀየር ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል።

የምንመኛትን ውብና ጠንካራ ሀገር ለመፍጠር የፅዳት ባህላችንና የአካባቢ ጥበቃ ተሳትፏችን ማደግ አለበት። የዚህ ውጤት ቱሩፋቱ ብዙ ነው፡፡ ከቱሩፋቶቹ መካከል በተፈጥሮ፣ በታሪክ፣ በባህል እና በሌሎች ፀጋዎቻችን አማካኝነት ከቱሪዝም ዘርፍ የበለጠ ተጠቃሚ መሆን የሚያስችለው ይገኝበታል። ለመጪው ትውልድ ንፁህና ጠንካራ ሀገር ከማስረከበ ባሻገር ልክ እንደ ጃፓንና ሌሎች የዓለማችን ሀገራት ንፅህናንና አካባቢን የመጠበቅ ተግባር የማንነታችን መገለጫ ሆኖ እንዲታወቅ እድል ይፈጥራል።

በኢትዮጵያ በደካማ የቆሻሻ አወጋገድ እና ውበት አጠባበቅ የሚታወቁት ከተሞቻችን ብቻ አይደሉም። እስካሁን ትኩረት አላደረግንባቸውም እንጂ ፣ ችግሩ ወደ ውብ ተፈጥሮዎቻችን እና የቱሪዝም መዳረሻዎቻችን አካባቢ ተዛምቷል። ንቅናቄው እነዚህን አካባቢዎችንም እንዲታደግ ለማድረግ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ በተፈጥሮ ሀብቷ ታድላለች። በርካታ ፓርኮች እንዲሁም ጥብቅ ስፍራዎች በጉያዋ ይዛለች። በዚህ የተነሳ ቱሪስቶች የጉዞ እቅድ አውጥተው ወደ ተለያዩ መዳረሻዎቿ በመዝለቅ ይጎበኟታል። እነዚህ ጎብኚዎች መልካም ነው፤ ይሁንና ወደ ስፍራው ሲያቀኑ ከአካባቢ ጋር የማይስማሙ እንደ ፕላስቲክና የመሳሰሉት በካይ ቁሶችን ወደ ፓርኮቹ በሚወስዱ አካባቢዎች፣ በፓርኮቹና መስህብ ስፍራዎቹ ላይ ይጥላሉ። ይህ ችግር እየተስፋፋ መጥቷል።

ጎብኚዎች ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚና ገፅታ የሚኖራቸው ፋይዳ እንዳለ ሁሉ፣ ከላይ ያነሳናቸውን አይነቶች አሉታዊ ጎኖችንም ያሳድራሉ። በካይ ቁሶች በአልባሌ ቦታ ላይ ያለ ከልካይ መጣላቸው በቤትና የዱር እንስሳት፣ ሃይቆች፣ አእዋፋትና ብርቅዬ የሆኑ ሀብቶቻችን ላይ ጉዳት ያስከትላሉ። ይህ ድርጊት የውጪ ሀገር ጎብኚውን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ የሀገር ውስጥ ጎብኚንም ይመለከታል። በመሆኑም ከወዲሁ ጥብቅ ሕግ ማበጀት በመዳረሻ ስፍራዎች ላይ የቆሻሻ አወጋገድና የመፀዳጃ አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

ጽዱ ኢትዮጵያ ነገ የምንመኛትን ውብ ሀገር ለመገንባት የሚያስችል መሠረት ይጥላል። ከግለሰብ እስከ ተቋም ርብርብ ሲደረግ እና በአንድነት ለአንድ አላማ ሲሰራ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ለውጥ ማምጣት ይችላል። ይህን መሰል ንቅናቄ የአንድ ጊዜ ብቻ እንዳይሆን እንደ ባህል እንዲሰርፅና ትውልድ የማንነቱ መገለጫ አድርጎ እንዲወስደው ደጋግመን ደጋግመን ልንተገበረው ይገባል የሚለው የዛሬው መልእክቴ ይሁን። **ሰላም!**

# ተጠየቅ

# «በውሃ ውስጥ የሚገኙ ማዕድናት መጠን መብዛት የንጹህ መጠጥ አቅርቦት ላይ ፈተና ሆኖብናል»

-ኢንጂነር ፊልታሞ ዲብሎ
በደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል የውሃ እና ማዕድን ቢሮ፣
የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ

መክሊት ወንድወሰን ፣ ሞገስ ተስፋ እና ሙሉቀን ታደገ

**የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ስውጡ ከመጣ ወዲህ እንደ አዲስ የተዋቀረ ክልል ነው፡፡ በክልሉ የተለያዩ ማዕድናት፣ በማር፤ በቡና እና በቅመማ ቅመም በስፋት ይገኛሉ፡፡ ክልሉ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ቀደም ብሎ ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮች አሁን ላይ በክልሉ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች፤ እንዲሁም የሕዝብን ጥያቄዎች በመመለስ ሂደት ላይ ጫና መፍጠራቸው ይነገራል፡፡**

**ለአብነትም፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በተፈለገው ልክ አለመኖር በክልሉ ሕዝብ በተደጋጋሚ የሚነሳ ቅሬታ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል የውሃ እና ማዕድን ቢሮ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ የሆኑትን ኢንጂነር ፊልታሞ ዲብሎ አነጋግረናል፡፡ መልካም ንባብ፤**

**አዲስ ዘመን፡- የቢሮው የ2016 በጀት ዓመት ክንውን ካቀዳችሁት አንጻር በምን መልኩ የሚገለጽ ነው?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** ቢሮው ሁለት ዘርፍና ሁለት ተጠሪ ተቋማት አሉት፡፡ የመጀመሪያው የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳይኒቴሽ ዘርፍ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የውሃ አስተዳደር ነው፡፡ በ2016 በጀት ዓመት በውሃ አስተዳደር ዘርፍ የተከናውኑ ተግባራትን ስንመለከት፤ በዘርፉ ሁለት ዳይሬክተሮች አሉት፡፡ አንደኛው የመጠጥ ውሃ ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች የሚያከናውን ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የውሃ ሀብት አስተዳደርን ሥራ የሚከውን ነው፡፡

በመጠጥ ውሃ ጥናትና ዲዛይን ዘርፍ ከተከናወኑ አብይ ተግባራት መካከል፣ የቦንጋ ከተማ ንፁህ የውሃ አቅርቦት አንዱ ነው፡፡ የቦንጋ ከተማ ንፁህ የውሃ መጠጥ አቅርቦት ችግር ያለበት ከተማ ነው። የመጠጥ ውሃ ጥናትና ዲዛይን ዘርፍ እንደ ቢሮ ከተቋቋመ በኋላ የከተማዋን የውሃ ችግር ለመፍታት የአጭር ጊዜ፤ የመካከለኛ ጊዜ እና የረጅም ጊዜ በሚል በሶስት ምዕራፎች አቅዶ እየሠራ ነው፡፡

ከረጅም ጊዜ እቅድ አኳያ የቦንጋ ከተማን የውሃ ችግር ሙሉ በሙሉ እና በዘላቂነት መፍታት የሚያስችል ነው፡፡ ይህን እውን ለማድረግ ከፌዴራል ዲዛይንና ኮንስትራክሽን ሱፐርቪዥን ጋር የውል ስምምነት በመፈጸም ጥናቶችን አስጀምረናል። ከዚህ አኳያ በ2016 ዓ.ም ጥናቱን መቶ በመቶ ለማጠናቀቅ ታቅዶ ነበር፡፡ የዘጠኝ ወር አፈጻጸሙ ደግሞ 50 በመቶ ነው፡፡

ከረጅም ጊዜ እቅድ አኳያ ከተያዙ ፕሮጀክቶች መካከል ሌላው የሚዛን አማን ከተማን የውሃ አቅርቦት ማሻሻል የሚል ነው፡፡ የሚዛን አማን ከተማን የውሃ አቅርቦት ማሻሻል ከዚህ ቀደም የነበረውን የዲዛይን ማሻሻያ ክለሳ ‹‹ሪቪው›› ሥራ ሰርተናል፡፡ የተሻሻለውን የዲዛይን ሥራ ሰነድ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ልከናል።

ምክንያቱም ይህ ፕሮጀክቱ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ፕሮጀክቱን የሚመጥን ሀብት አፈላልጎ እንዲመድብ ለማድረግ ነው፡፡ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም በተሰጠው የተሻሻለ ጥናት መሠረት ለፕሮጀክቱ ሀብት እያፈላለገ ነው፡፡ የተፈለገው ሀብት በተገኘ ጊዜ የሚዛን አማን ከተማን የውሃ አቅርቦት ፕሮጀክትን ወደ ሥራ እናስገባለን፡፡

ሌላው በዚህ ዓመት ታቅዶ የነበረው ውሃን የማከም ሥራ ነው፡፡ ይህንንም መቶ በመቶ አከናውነናል፡፡ በቤሸኮ ‹‹የማዝ ፍሎራይድ ትሪትመንት›› የሚባለውም 76 በመቶ ተከናውኗል።

በመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳይኒቴሽን ዘርፍ 54 ፕሮጀክቶችን ለማከናወን ነበር ያቀደው፡፡ በፕሮጀክቶቹ ስር የተለያዩ ፕሮግራሞች አሉ፡፡ እንደ ሀገር በዘላቂ የልማት ግቦች የሚሰሩ 14 ፕሮግራሞች አሉ፡፡ በክልል መንግሥት በጀት ምድቦች የሚሰሩ አምስት የገጠር ውሃ ተቋማት አሉ፡፡ በዚህ ዓመት እነዚህን ሥራዎች ጨርሰን 90 ሺህ የሚሆነውን ማህበረሰባችንን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ፤ በዘጠኝ ወር ከ89 ሺህ 900 በላይ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በዚህም ክልሉን እንደ ክልል ስንረከብ የዓለም አቀፍ የጤና ድርጅትን መስፈርት አሟልቶ የነበረው የንጹህ ውሃ መጠጥ ሽፋኑ 31 በመቶ የነበረ ሲሆን፤ በባለፈው ዓመት ብቻ 39 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

ለማህበረሰባችን የንጹህ ውሃ ከማቅረብ በተጨማሪ በዘርፉ ለዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ነበር፡፡ በዚህም በዚህ ዓመት ለሦስት ሺህ ሥራ አጥ ወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር አቅደን በ9 ወራት ውስጥ ለሁለት ሺህ 500 ወጣቶች ጊዜያዊ እና ቋሚ የሥራ እድል መፍጠር ችለናል፡፡

በዚህ በኩል አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች እየተሰሩ ያሉት በብድር ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ፕሮጀክቶች በፍጥነት ተጠናቅቀው ወደ ሥራ በመግባት ብድሩን መመለስ አለባቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ለአራት የውሃ ፍሳሽ አገልግሎቶች የምዘና ደረጃ በመሥራት ወደ ሥራ ለማስገባት አቅደን ለሰባት ውሃ ፍሳሽ አገልግሎቶች የደረጃ ማሻሻያና ደረጃ ሰተናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ዓመት ከ89 ሺህ 900 በላይ የማህበረሰብ ክፍሉችን በንጹህ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ መደረጉን ገልጸዋል። በተጨባጭ የት እና በምን ያህል ገንዘብ የሚለውን ቢገልጹልን?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** በዚህ ዓመት የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ማግኘት ከቻሉ የክልላችን አካባቢዎች አንደኛው ተርጫ ነው፡፡ በተርጫ የንጹህ መጠጥ የውሃ ፕሮጀክት 268 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል። ይሄንን ጨርሰን አስመርቀናል። በዚህም 24 ሺህ ሰዎችን የንጹህ ውሃ መጠጥ አገልግሎት ማግኘት ችለዋል፡፡

ሌላው ደግሞ ዋቻ የንጹህ መጠጥ የውሃ ፕሮጀክት ነው፡፡ ለዚህም 223 ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገበት ነው፡፡ ይህም 36 ሺህ ሕዝብ ተጠቃሚ ማድረግ የሚችል ነው፡፡ በርግጥ አሁን ከተማዋ ላይ 36 ሺህ ሕዝብ የለም፡፡ ነገር ግን የከተማዋ እድገት ፈጣን ስለሆነ ፕሮጀክቱ በታሳቢነት 36ሺ ለሚሆን ሕዝብ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ የተሰራ ነው፡፡

ሌላው በዚህ በተጨባጭ የንጹህ ውሃ ተጠቃሚ መሆን የቻለው ደግሞ የቦንጋ ከተማ ነው፡፡ ከአጭር ጊዜ አንጻር በቦንጋ ከተማ ያለውን ከፍተኛ የሆነ የውሃ ችግር ለማቃለል ‹‹የኢመርጀንሲ›› ሥራዎችን ስናከናውን ነበር፡፡ በዚህም ከ70 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት ፕሮጀክት ነበር፡፡ ይህን ፕሮጀክት አጠናቀን አስረክበናል፡፡ በዚህም 13 ሺህ 200 የሚሆኑ የቦንጋ ከተማ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

‹‹ዋን ዋሽ›› ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር የተሰሩ እና ዘንድሮ ጀምረን ዘንድሮ የጨረስናቸው ፕሮጀክቶችም አሉ፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶችም በመጠናቀቃቸው ነው በድምሩ ከ89 ሺህ 900 በላይ የክልላችን ሕዝብ የንጹህ ውሃ መጠጥ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በግንባታ ላይ ያሉ እና ለመገንባት በእቅድ የተያዙ ፕሮጀክቶችን እንዴት ይገለጻሉ?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** በክልላችን በርካታ ግንባታቸው በሂደት ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች እና ለመገንባት በእቅድ ደረጃ የተያዙ አሉ። ግንባታቸው በሂደት ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች መካከል ዳውሮ ዞን የሚገኘው የላላ ፕሮጀክት አንዱ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በስኬት ፈንድ የሚሰራ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም 74 በመቶ ነው፡፡ ቀሪ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ የሚረዱ አብዛኛው እቃዎች ከውጭ የሚመጡ ናቸው፡፡ አሁን ላይ ግማሹ እቃ ሞጆ ላይ ይገኛል፡፡ ግማሹም ሳይት ላይ ደርሷል፡፡ በዚህ ዓመት ይጠናቀቃል፡፡

ሌላው ግንባታቸው በሂደት ላይ ከሚገኙ ፕሮጀክቶች መካከል የሚጠቀሰው በምዕራብ ኦሞ ላይ የሚገኘው ፕሮጀክት ነው፡፡ ይህን ፕሮጀክት ዘንድሮ ለማጠናቀቅ እየሠራን ነው፡፡ አሁን ላይ ፕሮጀክቱ 92 በመቶ ያህል ሥራው ተጠናቋል፡፡

በዚህ ረገድ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ፣ ከክልሉ በጀት ሲመደብ እኛ መሠረት የምናደርገው ሁለት ነገሮችን ታሳቢ አድርገን ነው፡፡ የመጀመሪያው የእኩል ተጠቃሚነት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሁሉም የክልሉ ዜጎች ክልሉም ሆነ ሀገሪቱ ከምታመነጫቸው ሀብቶች እኩል ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ ለማድረግ ይሰራል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ በክልላችን አንዱ ከሌላው አንጻር በልማት በእጅጉ ወደ ኋላ የቀረ ማህበረሰብ በመኖሩ ወደኋላ ለቀሩት የማህበረሰብ ክፍሎች ልዩ ድጋፍ እናደርጋለን፡፡ በዚህም ምዕራብ ኦሞ አካባቢ የሚገኙ አርብቶ አደሮችን ፍትሃዊ ተጠቃሚ ለማድረግ እና በልማት ወደኋላ እንዳይቀሩ ልዩ ድጋፍ በማድረግ ብዙ ፕሮጀክቶች ተጀምረው በመጠናቀቅ ላይ ናቸው።

ከንጹህ መጠጥ ውሃ ጋር ተያይዞ በክልላችን ‹‹ኮዋሽ›› የሚባል ፕሮግራም አለ፡፡ ይህ ፕሮግራም ሁለት ወረዳና አንድ ዞን ይይዛል፡፡ ይሄ 40/60 በሆነ ፕሮግራም የፊሊላንድ መንግሥትና የኢትዮጵያ መንግሥት በጋራ በመሆን የሚሰሩት ነው፡፡ 40 በመቶ ከፊሊላንድ መንግሥት፤ 60 በመቶ የሚሆነውን ወጪ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚሸፍነው ነው፡፡ ከፊሊላንድ መንግሥት የሚመጣው ድጋፍ ለስልጠና የምንጠቀመው ሲሆን፤ በኢትዮጵያ መንግሥት የሚሰጠውን ለኢንቨስትመንት እንጠቀመዋለን። በዚህ አንጻር በዚህ ዓመት 10 ለመሥራት አቅደን አምስቱ አገልግሎት እየሰጡ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ አምስቶቹም በተወሰነ ጊዜ ይጠናቀቃሉ፡፡

በ‹‹ኮዋሽ››ፕሮጀክት የፕሮጀክቶችን ጨረታ የሚያወጣው እና ሠራተኞችን የሚቀጥረው ህብረተሰቡ ነው፡፡ የኛ ሥራ የሚሆነው ‹‹ማች›› ወይም የወጪ መጋራትን ሥራ ማጠናቀቅ ነው። ማች ወይም ወጪ መጋራት ሥራ ማለት አንድን ፕሮጀክት ለመገንባት ይሄን ያህል ገንዘብ እኔ አለኝ፤ ቀሪ ይህን ያህል ገንዘብ ደግሞ ብትሰጡኝ አንድ ፕሮጀክት መገንባት እችላለሁ ብሎ የወጪ መጋራት የሚያስችል አቅም ነው፡፡

ከወጪ መጋራት በኋላ ያለውን ሥራ በህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲከናወን ሲደረግ ብዙ ጥቅሞች አሉት። በተለይ ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ የሚፈጠር ችግርን በቀላሉ መፍታት ያስችላል፡፡ ህብረተሰቡ የኔ ነው ብሎ ከጀመረው ቀጣይነቱ የዛን ያህል ነው። ከጉልበት አኳያ ብንመለከትም በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመት ወጪን ህብረተሰቡ በራሱ እንዲሸፍን ማድረግ የሚያስችል ነው፡፡ ወደፊት ሁሉም ፕሮጀክቶች በዚህ መልኩ ቢከናወኑ አዋጭ ይሆናሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከነባሩ ደቡብ ክልል ጋር እንደ ቢሮ ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል የሀብት ክፍፍል ሂደቱ እንዴት ይገለጹታል?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ማሽነሪዎች ስላልነበሩን በባለፈው ሁለት ዓመታት እንደቢሮ ሥራዎችን ለመሥራት ተቸግረን ነበር፡፡ ዘንድሮ የጥገና ማሽኖችን ከነባሩ ደቡብ ክልል በክፍፍል



ፎቶ- በረሀን ታደሰ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## «በውሃ ውስጥ የሚገኙ ማዕድናት...

ከገጽ 6 የዞረ



ማግኘት ችለናል፡፡ ይህም ሞባይል ጋራዥ እና መሰል ሥራዎችን በቀላሉ እንድናከናውን አስችሎናል፡፡

ከሀብት ክፍፍሉ በፊት የቴፒን ሕዝብ ውሃ የምታጠጣው አንድ ጉድጓድ ብቻ ነበረች፡፡ ነገር ግን አሁን ላይ በሀብት ክፍፍሉ ባገኘናቸው ማሽነሪዎች በመጠቀም ቴፒ ላይ ሶስት ተጨማሪ የውሃ ጉድጓዶችን መቆፈር ችለናል፡፡ ይህም ቴፒን ሕዝብ በአንድ ሴኮንድ ውስጥ ጊዜ 40 ሊትር ውሃ እንዲያገኝ አስችሎታል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የበጀት እጥረት እንዳለበት ይታወቃል።ከዚህ አንጻር ማቺንግ ፈንድ ወይም ወጪ ማጋራት እንዴት ለመሸፈን አቅዳችኋል?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** ክልሉ አዲስ የተደራጀ ክልል በመሆኑ የፋይናንስ ችግር አለበት፡፡ ያም ቢሆን ክልሉ የሚጠበቅበትን ማቺንግ ፈንድ እያዋጣ ነው፡፡ ነገር ግን ከተማ አስተዳደሮች እና ወረዳዎች የሚጠበቅባቸውን እና የሚፈለገውን ያህል ማቺንግ ፈንድ ያለማዋጣት ችግር አለባቸው፡፡

ከወጪ መጋራቱ በተጨማሪ የኮንትራክተሮች የአቅም ውስንነት፤ የግንባታ እቃዎች መናር፤ የበጀት እጥረት፤ የውጭ ምንዛሬ ችግር፤ የኮንትራት መዘግየት ያጋጥማሉ፡፡ ይህም የሕዝባችንን የንጹህ መጠጥ ውሃ ችግር መፍታት እንዳንችል እክል እየፈጠረብን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በቢሮው በቅንጅት ከመሥራት አንጻር ችግር እንዳለ ይነሳል። ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያላችሁን የቅንጅት አሠራር እንዴት ይገልጹታል?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** ቅንጅታዊ አሠራርን በሚመለከት ከፌዴራል ውሃና ኢነርጂ ጋር ጠንካራና ጥሩ ግንኙነት አለን፡፡ እነሱ ወርደው ይደግፉናል እኛም ድጋፍ ሲያስፈልግ ወደእነሱ እንሄዳለን፡፡

ከዞኖች ጋርም በትብብር እየሰራን ነው። ትላልቅ ፕሮጀክት ካልሆኑ በስተቀር የግንባታ ክትትልና የኮንትራት አስተዳደር ሥራዎችን ለዞኖች ነው የሚሰጠው፡፡ የዞኖን ባለሙያዎች በሚሰሩት ፕሮጀክቶች ላይ ተሳታፊ ሆነው የማሽነሪዎችን ተከላ ካልተመለከቱ በሜንቴናስ ኦፕሬሽን ላይም ችግር ይፈጠራል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ አጠቃላይ የግንባታ ክትትልና የኮንትራክት አስተዳደር ሥራ ለዞኖች ነው የሰጠነው፡፡ የተሰራውን ሥራ የሚለኩት፤ ክፍያ አጽድቀው የሚልኩትም ዞኖች ናቸው፡፡ ሌሎች ከባድ ሥራዎች ሲኖሩ ክልሉ በተለያየ ደረጃ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር በጣም በመናበብ የምንሰራው ይሆናል፡፡

በክልሉ ላይ አርብቶ አደርና ቆላማ አካባቢ የሚባል ቢሮ አለ፡፡ እነሱም የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ ስለሚሰሩ እንደግፋለን፣ እንናበባለን። እነሱ በአጠቃላይ አርብቶ አደር ላይ የሚሰሩት የንጹህ ውሃ አቅርቦት ሥራዎች ደጋፊ በመሆናቸው እንደጋገፋለን። ባጠቃላይ መንግሥታዊ ሆኑ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመናበብ ሥራዎችን እያከናወን ነው። ፕሮጀክቶችን ማንም ቢሰራቸው ህብረተሰቡን የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ የሚያደርጉ እስከሆኑ ድረስ የጋራ ስምምነት እናደርጋለን፤ ዶክመንት እንገመግማለን፤ በቅንጅት እንሰራለን፡፡ ነገር ግን ክልሉ በቂ የሰው ኃይል እጥረትና የሎጂስቲክስ እጥረት አለበት፡፡

በርግጥ አንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ ተደጋግፎ ከመሥራት አንጻር ክፍተቶች አሉ፡፡ በተለይ በሚዛን አማን የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ላይ ክፍተት ተፈጥሯል፡፡ ፕሮጀክቱ ትልቅ ሀብት የሚፈልግ ሆኖ ሳለ ይህን ፕሮጀክት ለማስቀጠል የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ለማነጋገር ብንሞክርም ሊደግፈን የሚችል አካል ግን አልተገኘም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ቦንጋ ላይ ያለው ፕሮጀክት ግንባታው ካለቀ በኋላ የአይረን ልኬቱ ችግር እንዳለበት ሰምተናል፡፡ ይህ ችግር አሁን ምን ደረጃ ላይ ነው?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** ችግሩ ሙሉ በሙሉ አልተፈታም፡፡ ይህ ችግር ያጋጠመው ቦንጋ ላይ ብቻ አይደለም፡፡ ክልሉ የውሃ ችግር የለበትም። የከርሰ ምድርም ሆነ ገጸ ምድርም ውሃ በበቂ አለው፡፡ ነገር ግን በከርሰ ምድርም ሆነ በገጸ ምድሩ ላይ የሚገኘው ውሃ ለመጠጥነት ከሚያስፈልገው መጠን በላይ ማዕድናት አለባቸው፡፡ በውሃ ውስጥ የሚገኙት የማዕድናት መጠን መብዛት ለክልሉ የንጹህ ውሃ መጠጥ አቅርቦት ፈተና ሆኖበታል፡፡

ለምሳሌ፣ ከፋ እና ዳውሮ ላይ የብረት መብዛት፤ ሸኮ ላይ የብረት እና ፍሎራይድ መጠን መብዛት ለንጹህ ውሃ አቅርቦቱ ማነቆ ሆኖብናል፡፡ የቦንጋ ውሃ ላይ የነበረውን የብረት መጠን ወደሚፈለገው ደረጃ ለማምጣት በርካታ ሙከራዎች አድርገናል። ግን አልተሳካም፡፡ በመሆኑም በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጨረታ ወጥቶ ጨረታውን አንድ የጀርመን ተቋራጭ አሸንፎ ነበር፡፡ የተወሰኑ ሥራዎችን ጀምሮ ነበር፡፡ ነገር ግን የጀርመን ኮንትራክተር ሥራዎችን አጠናቀኩ ካለ በኋላ የብረት መጠኑ በድጋሜ ሲመረመር ወደ ስታንዳርዱ አልመጣም፡፡

በመሆኑም የጀርመኑ ድርጅት ከህንድና ከኔዘርላንድ ሰብኮንትራክተር አስመጥቶ ሞክሮ ነበር። መሃል ላይ ኮሮና ሲመጣ ድርጅቱ ሥራውን ጥሎ ወጣ፡፡ አሁን ላይ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የግንባታ ሥራውን ለአርባ ምንጭ ከተማ ውሃ አገልግሎት የማማከሩን ሥራ ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እንዲሰሩ ሰጥቷል የሚል መረጃ ነው ያለን፡፡

በዓለም የጤና ድርጅት በውሃ ውስጥ የሚገኘውን የአይረን መጠን ተብሎ የተቀመጠው 0.3 እና ከዛ በታች ነው፡፡ ከዛ በላይ ከሆነ ለአገልግሎት አይመከርም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የቦንጋ የውሃ ጉድጓድ በስንት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ነበር የታቀደው? ምን ያህል ወጭስ ወቶበታል?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** አጠቃላይ ሥራዎቹ እኛ እንደ ክልል ከመምጣታችን በፊት የተጀመሩ ናቸው። በምን ያህል ገንዘብ እና መቼ መጠናቀቅ አለበት የሚለውን ለማወቅ መረጃዎችንም ለማግኘት ጥረት አድርጌ ነበር፡፡ ግን አልተሳካልኝም፡፡

የቦንጋ ውሃ ዲዛይኑ ከተሠራ ከ15 ዓመት በላይ ሆኖታል፤ የግንባታውም ሂደት ቆይቷል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የተለያዩ የውጭ እና የውስጥ ኮንትራክተሮች እየተፈራረቁ ሰርተዋል፡፡ ለምሳሌ ሾዶብ፣ ደቡብ፣ ወላይታ ውሃ አገልግሎት እና ሌሎች በርካታ ድርጅቶች እየተፈራረቁ ሰርተዋል። በመሆኑም ግልጽ የሆነ ፋይናንሻል ስቴትመንት አላገኘንም፡፡ ፋይናንሻል ስቴትመንቱን ለማግኘት በርካታ ጥረቶችን አድርገን ነበር፤ ግን አልተሳካም።

ቦንጋ ላይ ወደ አራት የሚሆኑ ጉድጓዶች የተቆፈሩ ቢሆንም፤ አንዱ ከፍተኛ አይረን ስላላው ታሽጎ ነው ያለው፡፡ ሌሎቹ ሶስቱም ቢሆኑ ከነችግሮቻቸው ነው ያሉት፡፡ እስካሁን ለነዚህን አራት ጉድጓዶች ወጪ የተደረገውን ሀብትም ማወቅ አልተቻለም፡፡

የግንባታው አጠቃላይ ወጪ ለማወቅ ከዞን እስከ ፌዴራል የሚገኙ የተለያዩ አካላትን አነጋግረን ነበር፡፡ ነገር ግን በየጊዜው ተጫራቾች ስለሚፈራረቁ ፋይናንሻል ስቴትመንት ለማግኘት አልቻልንም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በ2016 የበጀት ዓመት የክልሉ ቢሮ ምን ያህል በጀት ተበጅቶለታል? ምን ያህሉስ ሥራ ላይ ውሏል? ከአበዳሪ አካላትስ ምን ያህል ተገኝቷል?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** ክልሉ በዘንድሮ በጀት ዓመት ለንጹህ መጠጥ ውሃ ዘርፍ ተጠሪ ተቋማትን ሳይጨምር 120 ሚሊየን ብር መድቧል። ይሄ ቁጥር ክልሉ ካለው በጀት አንጻር ትልቅ ቁጥር ነው። ፕሮጀክቶቹ ከሚፈልጉት በጀት አንጻር ሲታይ ያነሰ ይመስላል፡፡ ሆኖም የክልሉ መንግሥት ለውሃ ዘርፉ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራ ነው ያለው፡፡

እውነት ለመናገር በክልል ደረጃ ከፍተኛ በጀት የተመደበው ለእኛ ቢሮ ነው፡፡ ነገር ግን ያደሩ ችግሮች አሁን ለምንሰራቸው ሥራዎች ችግር እየፈጠሩ ነው። ለዚህ ክልልም መመሥረት ዋነኛው ምክንያት ፍትሃዊ የመልማት እድል ባለመኖሩ ነው፡፡ በልማት ወደኋላ የመቅረት ችግር ነው፡፡ ከቀድሞው ክልል ሲንከባለሉ ከመጡ ችግሮች ጋር ተዳምሮ አሁን የክልሉ መንግሥት ያለው ውስን ሀብት መሠረተ ልማቶችን በተፈለገው ልክ ለማስኬድ አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ አዲሱ ክልል ለውሃ ዘርፉ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰቶት እየሰራ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የክልሉን የመጠጥ ውሃ ሽፋን ምን ያህል ለማድረስ አቅዳችኋል?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** በፌዴራልና በክልል ደረጃ ግልጽ የሆነ የስትራቴጂክ እቅድ አለ፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ በ10 ዓመት ውስጥ ሙሉ በሙሉ የመጠጥ ውሃ ሽፋን ለማዳረስ ታቅዷል፡፡ ክልሉም ይሁንኑ እቅድ ለማሳካት የራሱን እቅድ አዘጋጅቷል። ነገር ግን በየዓመቱ የታቀደውን እቅድ ለማሳካት የሚመጣው ሀብት በቂ መሆን አለበት፡፡ በነገራችን ላይ የመጠጥ ውሃ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ስለሆነ በሕዝብ ሞቢላይዜሽን ካልታከለበት በመንግሥት ወጪ ብቻ ማሳካት አይቻልም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ላይ ኢንቨስተሮች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ምን ጥረት እያደረጋችሁ ነው?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** እኛ እንደክልል ብሩህ ተስፋ ያለን ነን፡፡ በርካታ ያወቅናቸውና ያላወቅናቸው ሀብቶች አሉን፡፡ ክልሉ በማር ምርት አንደኛ ነው። በወርቅ ምርት ሁለተኛ ነው። የድንጋይ ከሰል ማምረት ተጀምሯል፡፡ በክልሉ በርካታ ሀብት አለ፡፡ ግን እስካሁን በተፈለገው ልክ ጥቅም ላይ አልዋለም። የክልሉ መንግሥትም ባለሀብቶች መጥተው እንዲኀበኙ እና ኢንቨስት እንዲያደርጉ ሥራዎችን እየተሰሩ ነው፡፡

ለምሳሌ ወደ ምዕራብ ኦሞ በሁለትና በሶስት ዓመታት ውስጥ ትልቅ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ ከፍተኛ ባለሀብቶች መተው ወደ ሥራ እየገቡ ነው፡፡ ለወደፊት ግን ክልሉ ቀድሞ ማደግ የሚችል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ቢሮው ያለበትን የሰው ኃይል ችግር ለመፍታት ምን እቅድ ይዛችኋል?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** ሰው ለመቅጠር ሀብት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ለሚቀጥሉት ዓመታት ሌላ የሰው ኃይል ከመቅጠር ይልቅ በታችኛው መዋቅር ውስጥ ያለውን የሰው ኃይል ለመጠቀም አቅደናል፡፡ ወረዳዎቹ አዲስ ስላልሆኑ እዚያ ያለውን የተደራጀውን የሰው ኃይል መጠቀም ያስፈልጋል። ያለንን የሰው ኃይል በአግባቡ እና በቅንጅት መጠቀም ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ ሀብት እስኪያፈራ ድረስ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሥራውን ጉዳይ እንዴት ልታደርጉ አስባችኋል ?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** በክልሉ ያለው በአብዛኛውን ሕዝብ ውሃ እየጠጣ ነው፡፡ አሁን ምን ዓይነት ውሃ እየጠጣ ነው ያለው? የሚለው ነው ጥያቄው፡፡ እኛ እንደ ክልል እቅደን እየሠራን ያለነው ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁት ላይ ብቻ ሳይሆን በቀላል ወጪ በመሥራት ተደራሽ ሊሆኑ የሚችሉትን እንደ ምንጮች ያሉ አማራጮች ላይ ነው፡፡ ምንጮች ላይ ማዕድናት አይበዙም፡፡ ማዕድናት የሚበዙት በከርሰ ምድር ውሃ ላይ ነው፡፡

በስትራቴጂክ እቅድ ላይ አቅምን ማገናዘብ ስለሚያስፈልግ እኛ ቅድሚያ የምንሰጠው በምንጭ ውሃዎች ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም የምንጭ ውሃ አንደኛ በቀላል ወጪ ይሰራል፤ ሁለተኛ ቀጣይነት አላቸው፤ ሶስተኛ ተደራሽ ናቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ወንዞችንስ አጣርቶ ለመጠቀም ምን እቅድ አለ?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** የወንዝ ውሃ መታከም (ትሪትመንት) ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ወንዝ በባህሪው ማኔጅ ማድረግ ይከብዳል፡፡ ብዙ ነገር ወደ ወንዝ ሊገባ ይችላል፡፡ ነገር ግን ለወደፊቱ የቦንጋን ውሃ ችግር ለመፍታት ጉማ የሚገባውን ወንዝ ለመጠቀም አስበናል፤ ዲዛይንም እያደረግን ነው፡፡ እንደ ለገዳዲ እና እንደ ገፈርሳ የወንዝ ውሃን በመጠቀም የንጹህ ውሃ ለማቅረብ፤ አሁን ማሻ ላይ ወንዝን ማልማት ጀምረናል፡፡ ግን የወንዝ ሥራው ከፍተኛ ካፒታል ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በቀላሉ የመጠጥ ውሃ መሆን የሚችሉ ምንጮች ላይ እየሰራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ቦንጋ የክልሉ መቀመጫ እንደመሆኗ የቦንጋ የውሃ ችግር መቼ ይፈታል?**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** ሙሉ በሙሉ የሚፈታው እኛ እያካሄድን ያለነው ጥናትና ዲዛይን ሙሉ በሙሉ አልቆ ሀብት ስናገኝ ነው፡፡ ዲዛይኑ በዚህ ዓመት ያልቃል፡፡ የሚፈልገው ሀብትም ከአንድ ቢሊየን ብር በላይ ይሆናል የሚል ግምት አለን፡፡ ሀብት ባገኘን ጊዜ ወደ ሥራ እንገባለን፡፡ ነገር ግን እስከዚያ ድረስ በገጸ ምድር ውሃ ጉማ ወንዝ አክሞ በመጠቀም ችግሩን ለማቃለል እቅድ አለ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡**

**ኢንጂነር ፊልታሞ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# የፕሪቶርያው ስምምነትና የማዕከላዊ መንግሥቱ ጥረት

**አሊሴሮ**

ለሁለት ዓመታት ያህል በመንግሥትና በሕወሓት መካከል ሲደረግ የነበረው ጦርነት ጥቅምት 23 ቀን 2015 በፕሪቶርያ በተካሄደው የሰላም ስምምነት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን መሠረት አድርጎ ሉዓላዊነትን፣ የግዛት አንድነትን እና ብሔራዊ ጥቅምን ባከበረ መልኩ ዕልባት አግኝቷል፡፡ የተደረሰው ስምምነት ደም አፋሳሹን ጦርነት ለማስቆም፣ እርዳታ እና መሠረታዊ አገልግሎቶች ለማስጀመርና የሀገሪቱን የድንበርና የግዛት አንድነት እንዲሁም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲከበር የማድረግ አላማ አለው።

በአጠቃላይ ሲታይ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ የተፈረመው የሰላም ስምምነት እንዲሁም ይህንን ተከትሎ በኬንያ ናይሮቢ የተፈረመው ባለ 12 ነጥብ የማስፈጸሚያ ሰነድ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች የያዘ ነው፡፡

የመጀመሪያው ጉዳይ ሕግ መንግሥታዊ ሥርዓትን ማስከበር ነው፡፡ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የሚመነጭ ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 102 በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲካሄድ የማድረግ ስልጣን ያለው የምርጫ ቦርድ እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ከዚህ ድንጋጌ በተቃረነ መልኩ በትግራይ ክልል «ምርጫ» ተካሂዷል በሚል የትግራይ መንግሥት መቋቋሙን ስሁት በሆነ መልኩ ለማወጅ መሞከሩ የሚታወስ ነው፡፡ በወቅቱም የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ የተካሄደውን «ምርጫ» እንዳልተካሄደ እንደሚቆጠር በመግለጽ ተቀባይነት እንደሌለው አስታውቆ ነበር፡፡

ይህንኑ ሃሳብ የሚያጸና ውሳኔ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ በተካሄደው ስምምነትም ሰፍሮ እናገኘዋለን። ምርጫው ሕገ ወጥ በመሆኑም በትግራይ የሽግግር መንግሥት ይቋቋማል፤ በሂደትም ምርጫ ተካሂዶ ክልሉን የሚያስተዳድር መንግሥት ይጸናል፡፡ ስለሆነም አሁን ባለው ሁኔታ የትግራይ ሕዝብን ሰላም የሚያስጠበቅውና ሕጋዊ ውክልና ያለውም የፌዴራል መንግሥት ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በትግራይ ሕዝብ ተመርጫለሁ የሚል ሕጋዊ አካል የለም፡፡ ስለሆነም ከዚህ ውጭ የሚቀርቡ ጉዳዮች በፕሪቶርያው ስምምነት መሠረት ተቀባይነት የላቸውም፤ በዚህ ጉዳይ ሊቀመጥ የሚችል ቅድመ ሁኔታም እንደሌለ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡፡

በሌላ በኩል የፕሪቶርያው ስምምነት በግልጽ ካስቀመጣቸው ነጥቦች መካከል በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ መከላከያ ሠራዊት ብቻ መኖር አለበት የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በስምምነቱ ላይ ዋነኛ ጉዳይ የሆነውን ትጥቅ ማስፈታትን በተመለከተ ሁለቱም ወገኖች በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ የመከላከያ ኃይል ብቻ እንዳለ ከስምምነት የደረሱበት ጉዳይ ነው።

ይሄንን እውነታ ወደጎን ትቶ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ለማጓተት መሞከር አይቻልም። በፕሪቶርያው ስምምነትም ሆነ በናይሮቢው የማስፈጸሚያ ሰነድ መሠረት ስምምነቱን ወደ ተግባር ከመለወጥ ውጭ ሊቀመጥ የሚገባ ቅድመ ሁኔታ አይኖርም፡፡

ሌላው በፕሪቶርያው ስምምነት የፌዴራል መንግሥትና ሕወሓት ውሳኔ ካሳለፉባቸው ጉዳዮች መካከል የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን የማስጠበቅ ስልጣን የኢትዮጵያ መንግሥት ብቻ እንደሆነ ነው፡፡ በተለይም ከውጭው ዓለም ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችና ስምምነቶች ሁሉ ሊከናወኑ የሚችሉት በፌዴራል መንግሥት ብቻ መሆኑ ከስምምነት ላይ የተደረሰበት ነጥብ ነው፡፡ ይህው ሃሳብም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 8 ላይ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ የፕሪቶርያው ስምምነት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚያጸናና የዜጎችን ሰቆቃ የሚቀርፍ ስምምነት በመሆኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚተገበር ነው፡፡ ስምምነቱ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ

> **በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ዋነኛው መፍትሔ የፕሪቶርያውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ መሆኑን የኢፌዴሪ መንግሥት በጽኑ ያምናል። ይሄንንም በተመለከተ የፌዴራሉ መንግሥት ከመነሻው እስካሁን ያለው አቋም ወጥ እና የማይናወጥ መሆኑን ገልጿል**

የነበሩትን የትግራይ፤ የአማራና የአፋር ሕዝቦችን እፎይታ አጎናጽፏል፡፡

ከፕሪቶርያው ስምምነት ቀጥሎ የተካሄደው የናይሮቢ ስምምነት መተማመንን የፈጠረና ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሰላም መንገድ የሚያጸና ነው፡፡ በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የተቋረጡ መሠረተ ልማቶችንና ሰብዓዊ ድጋፎችን በሚፈለገው መልኩ ለማድረስ መሠረት የጣለ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም በትግራይና በአማራ ክልሎች አንዳንድ አካባቢዎች ተቋርጠው የነበሩ የቴሌኮሙኒኬሽን፤ የኤሌክትሪክና የባንክ አገልግሎቶች መልሰው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ለማድረግ አስችሏል፡፡ የሕዝቡን ችግር በፍጥነት ለመቅረፍም አሁንም ድረስ ሥራዎች በስፋት እየተሠሩም ይገኛሉ።

ሌላው የፕሪቶርያው ስምምነት የማዕዘን ድንጋይ ግጭትን በዘላቂነት ማስቆም ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕወሓት በደቡብ አፍሪካ ለ10 ቀናት ከመከሩ በኋላ በዘላቂነት ግጭት ለማቆም ተስማምተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን ለማረጋገጥ በርካታ መስዋዕትነት የከፈለ ሕዝብ ነው፡፡ በመስዋዕትነቱም የሀገሩን ሉዓላዊነት አጽንቷል፤ አንድነቱን አጠናክሯል፤ ዳር ድንበር አስከብሯል፡፡ የኢትዮጵያን መፍረስ ለሚመኙ ባዕዳን በቂ ትምህርት ሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ወደማይፈልጉት ጦርነት ከመግባታቸው በፊት በርካታ የሰላም ጥረቶችን ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ሽማግሌዎችንና ታዋቂ ሰዎችን ጭምር በመላክ ለሰላም ያላቸውን ፍላጎት በተደጋጋሚ ገልጸዋል፡፡ ከዚህም አልፎ ኢትዮጵያ አውዳሚው ጦርነት ውስጥ ሆና «የሰላም ያለህ» ሲሉ ቆይተዋል። ለሰላም ሲባል የትም ቦታ፤ በማንኛውም ጊዜና ርዕሰ ጉዳይ ለመወያየት ፍቃደኝነታቸውን ገልጸዋል፡፡ ጥረቱም ፍሬ አፍርቶ በመንግሥትና በሕወሓት መካከል ታሪካዊ የሚባል የሰላም ስምምነት ተፈርሟል፡፡

"በዘላቂነት የጦር መሳሪያ ድምጽ እንዳይሰማ ለማድረግ እና በሰሜን ኢትዮጵያ ለሁለት ዓመት የዘለቀው ግጭት እንዲቆም ተስማምተናል" ብለዋል ሁለቱ አካላት።

ሕወሓት እና መንግሥት በአንድ ድምጽ ግጭቱ ከፍተኛ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሳራዎችን አስከትሏል ካሉ በኋላ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ከግምት በማስገባት ግጭቱን ምዕራፍ ከኋላችን ትተን "በሰላም እና በመቻቻል ለመኖር" ተስማምተናል ማለታቸው የሚታወስ ነው። በዚሁ መሠረት አንጻራዊ ሰላም ሰፍኖ ቆይቷል፡፡

የፕሪቶርያው ስምምነት ሌላኛው ማዕዘን ትጥቅ ማስፈታት ነው፡፡ የኢትዮጵን ሉዓላዊነት እና የግዛት አንድነት ማረጋገጥ እና መጠበቅ መሠረታዊ ጉዳይ ነው ያሉት ሕወሓት እና ኢትዮጵያ መንግሥት፤ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥትን ለማስከበር መስማማታቸው የሚታወስ ነው። የኢትዮጵያ ፌዴራል የፀጥታ ኃይሎች "በትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም የፌዴራሉን ተቋማትና አየር ማረፊያዎችንና አውራ ጎዳናዎችን ጨምሮ ዋነኛ መሠረተ ልማቶችን" ሙሉ ለሙሉ እንደሚቆጣጠሩ ተጠቅሷል።

ለተጎጂ ወገኖች ሰብዓዊ እርዳታን ማቅረብ ሌላኛው የፕሪቶርያው ስምምነት አካል ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሰብዓዊ ድርጅቶች ጋር በመሆን የሰብዓዊ ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው የተፋጠነ ርዳታ እንዲያደርስ ከመግባባት ላይ ተደርሷል።

ከላይ የተዘረዘሩት ዋነኛዎቹ የፕሪቶርያው ስምምነት አካል ሲሆኑ ስምምነቱ ከተፈረመበት ከጥቅምት 23 ቀን 2015 ጀምሮ ያለው አተገባበር ግን የተሟላ ነው ብሎ ለመውሰድ አያስደፍርም፡፡ በዚህ ረገድ ባለፈው አንድ ዓመት በስምምነቱ መሠረት የተፈጸሙ ጉዳዮችን እና ቀሪ ቤት ሥራዎች ምንድን ናቸው የሚለውን መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ዋነኛው መፍትሔ የፕሪቶርያውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ መሆኑን የኢፌዴሪ መንግሥት በጽኑ ያምናል። ይሄንንም በተመለከተ የፌዴራሉ መንግሥት ከመነሻው እስካሁን ያለው አቋም ወጥ እና የማይናወጥ መሆኑን ገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የፕሪቶርያው ከአቋም ባሻገር ተግባራዊ እንቅስቃሴም አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል፡፡ ከስምምነቱ በኋላ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተመራ የተለያዩ ተቋማት አመራሮች ያሉበትን ቡድን ወደ ትግራይ የላከው የፌዴራል መንግሥት ነው።

የፌዴራል መንግሥት ተቋማትና ክልሎች ለትግራይ ሕዝብ ድጋፋቸውን ያሳዩት ወዲያው ነው። የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች በመቀሌ ተገኝተው ለሕዝቡ ያላቸውን አጋርነት በማሳየት የሚቻላቸውን ድጋፍ በዓይነትና በገንዘብ አድርገዋል፡፡

በፕሪቶርያው ስምምነት መሠረት የገዢው ፓርቲ ሊኖረው የሚችለውን ድርሻ በመተው ሕወሓትና የታጣቂ አመራሮች ጊዜያዊ መንግሥቱን እንዲያቋቁሙ አድርጓል፡፡ ምክንያቱም ከልዩ ልዩ አካላት ተውጣጥተው በጊዜያዊ አስተዳደሩ ውስጥ የሚካተቱ አመራሮች እስኪተዋወቁና እስኪግባቡ ድረስ የትግራይ ሕዝብ የችግር ወቅት እንዳይራዘም በማሰብ ነው። በዚህም ለትግራይ ሕዝብ ሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ከፕሪቶርያው ስምምነት በላይ በመሄድ አረጋግጧል፡፡

በክልሉ ተቋርጦ የነበረውን የትምህርት ሂደት ለማስቀጠል ልዩ ልዩ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ የሰው ኃይልና የተቋም አቅም ግንባታ፣ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ላይ ሥልጠና፤ የዩኒቨርሲቲዎችን የአመራር ቦርድ የማደራጀት ሥራ ተሠርቷል፡፡ በትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም በኩል 165 ነጥብ 8 ሚሊየን ብር በዕቅድ ተካትቶ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ለአንደኛና ለሁለተኛ ሩብ ዓመታት ማስፈጸሚያ 517.9 ሚሊየን ብር በገንዘብ ሚ/ር በኩል ለክልሉ ተልኳል፡፡

በትምህርት ላይ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት አንድ ነጥብ 46 ቢሊየን ብር ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፣ በ2016/17 ዓ.ም በትምህርት ቤቶች ላይ ለሚሠሩ ሥራዎች የ111 ነጥብ 08 ሚሊየን ብር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ የትምህርት ተቋማት መልሶ ግንባታ 441 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር ድጋፍ ተደርጓል።

የሞሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ወደ ሥራ ተመልሷል። በፋብሪካና በባህላዊ መንገድ ወርቅ የሚያመርቱ አካላትን በመደገፍ ሥራ ጀምረዋል፡፡ ለወርቅ ሥራ የሚያገለግሉ ሁለት ከባድ ተሽከርካሪዎች በርዳታ ተለግሰዋል፡፡

በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል የክልሉን የዘርፍ መሥሪያ ቤት ለማጠናከር ከተወሰዱ ርምጃዎች ባሻገር ለካፒታል በጀት አራት ነጥብ 9 ቢሊየን ብር፤ ለመደበኛ በጀት 11 ነጥብ 4 ቢሊየን ብር፣ እንዲሁም ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ 400 ሚሊዮን ብር፤ በድምሩ 16 ነጥብ 7 ቢሊየን ብር በ2015/16 ለክልሉ ተሰጥቷል፡፡ በክልሉ ለሚገኙ አራት ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ በድምሩ 5 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ተላልፎላቸዋል፡፡ በልማት አጋሮች በኩል ደግሞ የአንድ ነጥብ 7 ቢሊየን ብር ድጋፍ ለትግራይ ክልል እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህም በተጨማሪ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በቻናል አንድ አንድ ነጥብ 7 ቢሊየን እንዲሁም በገንዘብ ሚኒስቴር በክልሉ ባቋቋመው ጽሕፈት ቤት በኩል፣ በትግራይ ለሚከናወኑ የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች እና ለአየር ንብረት ለውጥ ፕሮጀክቶች በድምሩ ከ565 ሚልየን ዶላር በላይ ፈሰስ ተደርጓል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ ፕሮጀክትም 65 ሚሊዮን ብር ለክልሉ ተላልፏል።

በጦርነቱ ወቅት የተቋረጡ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችንም በልዩ ፕሮግራም የክልሉ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ለዘጠኝ ከተሞች የፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል ከ409 ሚሊየን ብር በላይ እና ከ7 ሚሊየን ዶላር በላይ ለክልሉ ተላልፏል፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርም ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ እና ለመንገድ ፕሮጀክት ጥገና ከ418.6 ሚሊየን ብር በላይ ወደ ክልሉ ልኳል፡፡ ለትግራይ ገጠር መንገድ ጥገና ከመንገድ ፈንድ ከብር 107 ሚሊየን ብር በላይ፤ የ2026 በጀት ቅድመ ክፍያ ከ50 ሚሊየን ብር በላይ ተልኳል፡፡ በፕላንና ልማት ኮሚሽን በኩል ደግሞ በጠቅላላው የ4.2 ሚሊየን ብር ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የክልሉን የጤና ዘርፍ አቅም ለመገንባት እንዲቻል 164 ልዩ ልዩ ባለሞያዎች ተመድበው ድጋፍ እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡ ሁሉንም በክልሉ የሚገኙ የጤና ተቋማት በመደገፍ ወደ አገልግሎት ለመመለስ የተቻለ ሲሆን፣ ሁሉም ሆስፒታሎች ተኝቶ የማከም አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ተችሏል፡፡ በክልሉ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎችን መልሶ ወደ ሥራ ለማስገባት በተደረገው ሁለገብ እንቅስቃሴ 217 ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት ተችሏል፡፡

በ2015/16 13 ነጥብ 4 ሚሊየን ኩንታል ማዳበሪያ ለክልሉ የቀረበ ሲሆን፣ ለአንድ ሺህ 427 አርሶ አደሮች መጠቀሚያ የሚሆን አንድ ሺህ 720 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በዚሁ የምርት ዘመን ፕሮጀክቶች በኩል ለክልሉ ተገዝቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በ2015/16 የምርት ዘመን ክልሉ 80 ሺህ የተለያዩ ማዳበሪያዎች ጠይቆ ሁሉም ቀርቦለታል፡፡ ለ2016/17 ምርት ዘመን ደግሞ ክልሉ ከጠየቀው መካከል የ70 ሺ ቶን ማዳበሪያ ተገዝቷል፡፡

ለግብርና መገልገያ የሚሆኑ የትራክተሮች፣ የውኃ ፓምፖች ድጋፍ ለአርሶ አደሮች ተለግሷል፡፡ በአጠቃላይ ከ37 ቢሊዮን ብር በላይ ለክልሉ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ይህ ድጋፍ ቀደም ሲል ለክልሉ ሲሰጥ ከነበረው አንጻር ከ5 ዓመታት በጀት በላይ ነው፡፡

በሕወሓት ወገን ግን አሁንም በበርካታ ሺ የሚቆጠር ታጣቂ ትጥቅ አልፈታም፡፡ ሠራዊት አልተበተነም፡፡ ግጭት ቀስቃሽ እና የጥላቻ ንግግሮች አልተቋረጡም። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ የፕሪቶርያውን ስምምነት የሚሸረሽሩና በሂደትም ወደ ግጭት ሊያስገባ የሚችል ነው፡፡ ስለዚህም ለሀገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መሠረት የሆነውና የዜጎች ሰቆቃ እንዲበቃ ያደረገው የፕሪቶርያው ስምምነት ቅድመ ሁኔታ የለውም፤ ስለሆነም በስምምነቱ መሠረት መፈጸም ከሁሉም ወገን የሚጠበቅ ግዴታ ነው፡፡ ያለውም ብቸኛው አማራጭ ይህንን ስምምነት ማስፈፀም ነው።

# የገበያ ትስስርን እና የልምድ ልውውጥን ለማሳካት ያለመው ኤግዚቢሽን

ወርቅነሽ ደምሰው

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ እንደመሆኗ በየጊዜው የተለያዩ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ኤግዚቢሽኖችንና ባዛሮች እያስተናገደች ትገኛለች፡፡ ባለፈው ሳምንት መጀመሪያም ስድስተኛውን ‹‹አግሮፉድና ፕላስትፕሪንት ፓክ ኢትዮጵያ 2024›› የንግድ ኤግዚቢሽንን በሚሊኒየም አዳራሽ አስተናግዳለች። ኤግዚቢሽኑ በግብርና፣ በምግብ፣ በመጠጥ፣ በፕላስቲኮች፣ በሕትመት እና በማሸጊያ ኢንዱስትሪ ላይ የተሰማሩ ዕውቅና ያላቸው ኩባንያዎች የተሳተፉበት ነው፡፡

ለሦስት ቀናት በቆየው አውደ ርዕይ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ12 ሀገራት የተወጣጡ (ቻይና፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ህንድ፣ ኢጣሊያ፣ ኬንያ፣ ታይዋን፣ ታይላንድ፣ ቱርክ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች እና እንግሊዝ) ኩባንያዎች) 122 ተሳታፊዎች ምርትና አገልግሎቶቻቸውን አቅርበዋል። አውደ ርዕዩ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚመክሩ ጉባኤዎችና የንግድ ልውውጦች ለመፍጠር ያስቻለም እንደነበር ተጠቁሟል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሀሰን መሐመድ እንደተናገሩት፤ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ምቹ አማራጮች አላት፡፡ በመንግሥት በኩል የግብርና የኢንዱስትሪ ምርቶች ምርታና ምርታማነት ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ በርካታ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በዚህም በምግብና በመጠጥ ማቀናበሪያና ማሸግ ላይ ለተሰማሩ ኩባንያዎች ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡

አውደ ርዕዩ በግብርና ምርቶች፣ በምግብና መጠጥ፣ በፕላስቲኮች ሕትመትና ማሸጊያ ኢንዱስትሪዎች ረገድ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አገልግሎቶች የቀረቡበት መሆኑን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው ፤ ይህም ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለሥራ ፈጠራ እና ለፈጠራ ሥራዎች መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ያልነበሩ ግብዓቶችንም ሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ እንደሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት እርስ በእርስ ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚረዳ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ አውደ ርዕዩ በሀገር ውስጥ ያሉ አምራቾች የሚያቀርቧቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ የሚያስችል ነው፡፡ በተለይ የንግድ እድሎችን ለማስፋት እና በኢንዱስትሪው ውስጥ ስላሉ አዳዲስ ለውጦች ግንዛቤ ለመጨበጥ ይረዳል። በተጨማሪም አዳዲስ ኢንቨስትመንት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲመጣ በማድረግ ምርትና ምታማነትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል።

በአውደ ርዕዩ ተሳታፊ ከሆኑ ድርጅቶች አንዱ ‹‹ጣና ድሪሊንግ ኤንድ ኢንዱስትሪ›› ኩባንያ ነው፡፡ አቶ ሳሙኤል ፍቅረ ‹‹በጣና ድሬሊንግ ኤንድ ኢንዱስትሪ›› ኩባንያ የሽያጭና ማርኬቲንግ ባለሙያ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚሉት፤ ድርጅቱ ማኑፋክቸሪንግ እና ከከርሰ ምድር ውሃን የማውጣት ሥራ ይሰራል፡፡ በዚህ ሥራ ላይ ከተሰማራ 15 ዓመታት አስቆጥሯል፡፡ ከእነዚህም በተጨማሪም ጥራቱን የጠበቀ ጥሬ እቃን ከውጭ በማስመጣት የፕላስቲክ ፓይፖችን ያመርታል፡፡ የፕላስቲክ ፓይፖች የማይዝጉ ከመሆናቸው የተነሳ ብረትን በመተካት ለመጠቀም ስለሚያስችሉ ጥራታቸውን የጠበቁ ፓይፖችን በማምረት ህብረተሰቡ በዘላቂነት እንዲጠቀሙበት እያደረገ ይገኛል፡፡

እነዚህ የፕላስቲክ ፓይፖችን ቢያንስ 50 ዓመታት ያህል አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል የሚለው አቶ ሳሙኤል፤ ድርጅቱ ከ20 ሚሊ ሊትር ጀምሮ እስከ 400 ዲያሜትር ድረስ ያሉ ፓይፖች እንደሚመረት ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም ፒፒሲዎችን በማምረት ለኮንስትራክሽን እና ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውሉ ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ እና ከኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ጋር አብረው እየሠሩ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ድርጅቱ ጥራታቸው ተፈትሾ የተረጋገጥ፣ ጥራታቸው የተጠበቁ እና ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ ምርቶች እያመረተ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ከከርሰ ምድር ውሃን ከተለያዩ ቦታዎች ለማውጣት እስከ 600ሜትር ጥልቀት ያላቸው ጉድጓዶችን ቁፋሮ በማካሄድ ውሃን ከከርሰ ምድር ያወጣል፡፡

ምርቶች የገበያ ተደራሽነታቸው የሰፋና ብዙ ፈላጊ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ በሚፈለገው ልክ ለማምረት በውጭ ምንዛሪ እጥረት የተነሳ ከውጭ የሚመጣው የጥሬ እቃ አቅርቦት እጥረት እያገጠመ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

‹‹ድርጅቱ ከውጭ የሚመጣ ምርቶችን በሀገር ውስጥ እንዲተኩ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ በሀገር ውስጥ ጥራት ያለው ከውጭ ከሚገባው የሚበልጥ ምርት ማምረት እየተቻለ፤ ከውጭ ለምን ይገባል በሚል ከፕላስቲክ ኤጀንሲዎች ጋር እየተነጋገር ሥራዎች እየሰራ ነው›› የሚሉት አቶ ሳሙኤል፤ ‹‹ከውጭ የሚመጡት ምርቶች ጥራታቸው ያልጠበቁ ስለመሆናቸው በድርጅቱ ስታንደርዱን በጠበቀ ላብራቶሪ ሆነ በተስማሚነትና ምዘና ኤጀንሲ ተመርምረው ሲፈተሹ ጥራታቸው ያልጠበቁና ከደረጃ በታች መሆናቸው ተደርሶባቸው ውድቅ እየተደረጉ ነው›› ይላሉ፡፡ ይህ ሀገር ውስጥ ማምረት እየተቻለ ከውጭ ማምጣት የገንዘብ እና የጊዜ ብክነት የሚዳርግ መሆኑን ማሳያ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ምርቶቹ ዓለም አቀፍ ጥራት ደረጃው በጠበቀ መልኩ ስለሚመረቱ ከውጭ ከሚመጡት ጋር ሲነጻጸሩ በዋጋቸው ከፍተኛና ብልጫ ያለው ነው ያሉት አቶ ሳሙኤል፤ የተሰሩበት ማቴሪያል አንዱ ዓይነት ሆነው የጥሬ እቃ አቅርቦቱ ከውጭ የሚመጣ መሆኑ ዋጋ ከፍ እንዲልና ከውጭ የሚገባ ደግሞ በዚያው ልክ ዋጋው ዝቅ እንዲል አድርጎታል ይላሉ፡፡

በምርቶቹ የተፈጠረው የገበያ ትስስር ጥሩ ቢሆንም ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ሲባል ህብረተሰቡ ቅድሚያ ለውጭው ምርት የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩን ጠቅሶ፤ የውጭ ምርቶቹን ገዝቶ የተጠቀሙ ደግሞ ከሀገር ውስጥ ምን ያህል ልዩነት እንዳለው ስለሚረዱ ከሁሉም በላይ የሀገር ውስጥ ምርቶችን የሚመርጡበት ሁኔታ መኖሩን ያመላክታል፡፡ ከውጭ የሚመጣው ምርት አንዴ ከተገዛ ለመመለስም አስቸጋሪ እንደሚሆን አንስተው፤ የሀገር ውስጥ አምራች ለሚያመርታቸው ምርቶች ኃላፊነት እንዳለበት አውቆ የሚሰራ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ድርጅቱ አብዛኛውን ጊዜ በተለያዩ አውደ ርዕዮች ላይ የሚሳተፉ ሲሆን፤ በስድስተኛው አግሮፉድና ፕላስትፕሪንት ፓክ አውደ ርዕይ ላይ ለአራተኛ ጊዜ እየተሳተፈ መሆኑን ያነሱት አቶ ሳሙኤል፤ የጥሬ እቃ አቅራቢዎች ጋር የተደረጉ ግንኙነቶችና የቢዝነስ እና ቢዝነስ ትስስር በማድረጋቸው የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው እድል እንዳመቻቸላቸው አመላክተዋል፡፡

አውደ ርዕዩ የገበያ ትስስርም ሆነ ተደራሽነትን ለማስፋት ያግዛል ያሉት አቶ ሳሙኤል፤ እንደዚህ ዓይነት ዓለም አቀፍ አውደ ርዕዮች ሲዘጋጁ በደንብ ቅስቀሳ ተደርጎላቸው ብዙ ሰዎች እንዲሳተፉበት ሆነ እንዲጎበኙ ማድረግን ይጠይቃል ሲል አስታወቀዋል፡፡

አቶ ሳሙኤል፤ ድርጅቱ ወደፊት አሁን ከሚያመርታቸው ምርቶች የተሻለ የማምረት አቅም እንዲኖረው በማድረግ ተጨማሪም

## ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ12 ሀገራት የተወጣጡ 122 ተሳታፊዎች ምርትና አገልግሎቶቻቸውን አቅርበዋል

ተፈላጊ የሆኑ የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት በሂደት ላይ መሆናቸው ይናገራሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን እነዚህ ምርቶች ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች በማጥናት ምቹ ሁኔታ ለመፈጠር የሚያስችሉ ሥራዎች እየሠሩ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

‹‹ኤች ዋይ ፊሊንግ›› የተሰኘ የቻይና ኩባንያ ሌላው የአውደ ርዕዩ ተሳታፊ ኩባንያ ነው። የኩባንያው የምስራቅ አፍሪካ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አቶ መንገሻ አስፋ እንደሚሉት፤ ኩባንያው ከቻይና ሀገር ማሽነሪዎችን በማስመጣት ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ጠርሙሶችን ያመረታል፡፡ ለስላሳ፣ ለጁስ፣ ውሃ፣ ለወተት አረቄ እና የመሳሰሉት ፈሳሽ ነክ ለሆኑ መያዣ የሚሆኑ ምርቶች ለማምረት የሚችሉ ማሽነሪዎች ያቀርባል፡፡ ማሽነሪዎቹ ቻይና ሀገር የሚሰሩ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ጨምሮ ለምስራቅ አፍሪካ ለማሽነሪዎቹ ሙሉ ቴክኒካል አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡

ኩባንያው በሀገር ውስጥ ካሉ ከፋብሪካዎች ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠር ብዙ ደንበኞችን ማፍራት የቻለ መሆኑን የሚገልጹት አቶ መንገሻ፤ በባለፈው ዓመት በአውደ ርዕዩ ተሳትፈው አቅም ካላቸው ፋብሪካዎች ጋር ኮንትራት የተፈራረሙበትና ሊፈራረሙ ያቀዱ ብዙ ደንበኞች ማፍራት ችለዋል፡፡ ከባለፈው ዓመት ተሞክሮ በመውሰድ በዘንድሮውም አውደ ርዕይ መሳተፍ ከቻሉባቸው ምክንያቶች መካከል ዋናዎቹ የተለያዩ ደንበኞችን በማፍራት ግብይት ለማስፋፋት እና ቴክኖሎጂውን ለማስተዋወቅ ነው፡፡ ይህ አውደ ርዕይ በርካታ ደንበኞች ለማፍራት የሚያስችልና የገበያ ተደራሽነትን የሚያሰፋ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ሀገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉት እቃዎችን አብዛኛው ጥሬ እቃ ከሀገር ውስጥ እንደሚወሰድ ነው አቶ መንገሻ የገለጹት፡፡ ‹‹ቀደም ሲል ውጭ ሀገር ተመርተው አልቆላቸው የሚመጡ ምርቶች መኖራቸው ጠቅሰው፤ አሁን ላይ ጥሬ እቃው ብቻ ከውጭ በማስመጣት ምርቶቹን ሀገር ውስጥ እንዲመረቱ እየተደረገ ይገኛል›› ይላሉ፡፡ ይህም መደረጉ ሁለት ነገሮችን ማስገኘት ያስቻለ ሲሆን የመጀመሪያው ያለቀ ነገር ከውጭ ሲመጣ የውጭ ምንዛሪ ፍጆታን ይጨምራል፤ ውጭውም በዚያኑ ያህል ያድጋል፤ ሁለተኛው ቴክኖሎጂ ሀገር ውስጥ ስለመጣ ጥሬ እቃ ሀገር ውስጥ ቢኖረን ሙሉ ለሙሉ ምርቱን በሀገር ውስጥ ማምረት የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል፡፡

‹‹Mingjia Packaging Machinery Technology ›› የተሰኘው የቻይና ኩባንያም የአውደ ርዕዩ ሌላው ተሳታፊ ነበር፡፡ የኩባንያው መስራች ሚስተር ኬቨን ጊን ኩባንያው በአውደ ርዕዩ እንደ ወተት፣ ጁስ ፣ እና የመሳሳሉ የለስላሳ መጠጦች የማሸጊያ ማሽን ይዞ መቅረቡን ይናገራሉ፡፡

ሚስተር ኬቨን ጊን እንደሚሉት፤ ኩባንያው የለስላሳ መጠጦችን ጥራታቸው በጠበቁ አልሙኒየም፣ ፕላስቲክ እና መሰል ማቴሪያሎች በተለያየ ዓይነትና ዲዛይን ለማሸግ የሚያስችል ማሽን እያስተዋወቀ ይገኛል፡፡ ማሽኑ የለስላሳ መጠጦች ከ125 ሚሊ ሊትር ጀምሮ እስከ 1000 ሚሊ ሊትር ድረስ የሚያሽግ ሲሆን፤ በሰዓት ከ3ሺ እስከ5ሺ የሚደርሱ ምርቶች ማሸግ ያስችላል፡፡

ሚስተር ኬቨን ጊን ኩባንያው በስድስተኛው አግሮፉድና ፕላስትፕሪንት ፓክ አውደ ርዕይ ላይ ሲሳተፍ የመጀመሪያ ጊዜ መሆኑን ጠቁመው፤ የለስላሳ መጠጦችን ማሸጊያ ማሽን ለአፍሪካ ለማስተዋወቅና ደንበኞችን የማፍራት ዓላማን ሰንቆ በአውደ ርዕዩ መሳተፉን ተናግረዋል፡፡ አውደ ርዕዩም ከብዙ ፋብሪካዎች ጋር ትስስር በመፍጠር እና የገበያ ተደራሽነታቸው ለማስፋት እንደሚያስችል ገልጸዋል፡፡

የ‹‹ወተር ፊት ጄነራል ትሬዲንግ›› የሽያጭ ባለሙያ ወጣት ሚኪያስ መንግሥቱ ድርጅቱ ከውሃ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሥራዎችን እንደሚሰራ ይናገራል፡፡ ኤች ዲፒ ፓይፓ የተሰኘ ለውሃ መስመር አገልግሎት የሚውል ከ20ሚሊ ሊትር እስከ 450 ሚሊ ምርት የሚይዝ ምርት ያመርታል፡፡ ድርጅቱ የማምረት አቅሙን ከዚህም በላይ ለማሳደግ ፕሮጀክት ተነድፎ እንቅስቃሴ መጀመሩን ያስረዳል፡፡

ምርቶቹን ለማምረት የሚውሉት ጥሬ እቃዎች ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶችና ከሌሎች ሀገራት የሚመጡ መሆኑን የሚገልጸው ሚኪያስ፤ ጥሬ እቃውን ከምንም ጋር ሳይቀላቀል ጥራቱን በጠበቀ መልኩ እንደሚመረት ይገልጻል፡፡

ድርጅቱ የሚያመርታቸው ምርቶች ጥራታቸው የጠበቁ ሆነው ከውጭ የሚመጣው በመተካት እየሰራ መሆኑን ጠቅሶ፤ እንደገናም ምርቶቹን ወደ ውጭ ኤክስፖርትም ለማድረግ አቅዶ ጥረቶች እያደረገ ሂደቶቹን መጀመሩን ይናገራል፡፡

ድርጅቱ ሀገር ውስጥ ፍላጎት መሙላት የሚያስችል አቅም እንዳለው የጠቀሰው ሚኪያስ፤ አሁን ላይ የፕላስቲክ ምርቶች ጥራታቸው እንደተጠበቀው ለረጅም ጊዜ የሚያገለግሉ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የብረት ምርቶች በፕላስቲክ እየተተኩ መሆናቸውን ይገልጻል። ህብረተሰቡም ግንዛቤ እያገኘ ምርቶችም ተቀባይነት እያገኙ በደንበኞች ዘንድ ተፈላጊ እየሆኑ መምጣታቸውን ያስረዳል፡፡

አውደ ርዕዩም የመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፉ መሆኑን ጠቅሶ፤ ምርቶችን በማስተዋዋቅ የገበያ ትስስር በመፍጠር፣ ከሌሎች አምራች ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እና ደንበኞችን ለማፍራት የሚያስችላቸው መሆኑን አመላክቷል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ዝርፊያ በየፈርጁ

**ዋስልኝ አየለ**

ለሰባት ሰዓታት ያህል (ከ2፡40 እስከ 9፡30) በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ግቢ ውስጥ በነበረኝ ቆይታ ብዙ ነገር ሳስተውል ውያለሁ፡፡ የሰልፉን ርዝመት፣ የሰዎችን ሕግና ደንብ ማክበር አለመላመድ.... በአጠቃላይ የነበረውን አሰልቺ የግቢው ውስጥ ወከባ ባለፈው ቅዳሜ ትዝብታችን አይተናል፡፡ ‹‹የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል›› እንዲሉ በእንዲህ አይነት ቦታዎች ላይ የማጭበርበር አይነቶች እንደሚኖሩ ግልጽ ነው፡፡ በዚያን ዕለት ያስተዋልኩትን የማጭበርበር አይነት ለማጋራት ወደድኩ።

የፓስፖርት አሻራና ፎቶ ለመስጠት የነበረው ሰልፍ ቀጥ ያለ ሳይሆን የተወለካከፈ ነበር፡፡ ሕንጻዎችንና መንገዶችን ሁሉ እያቋረጠ የሚቀጣጠል ስለሆነ በየቦታው ስብራቶች አሉት፡፡ ስለዚህ በየመታጠፊያው ‹‹የፓስፖርት አሻራ ሰልፍ ነው?›› እያሉ መጠየቅ የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም የሌላ ጉዳይ ሰልፍም ሊኖር ይችላል፡፡

ለማረጋገጥ በየመታጠፊያው ይህን እየጠየቅኩ መጨረሻው አካባቢ ደረስኩ፡፡ መጨረሻው አካባቢ ያሉትን ስጠይቅ፤ አንድ የባንክ ሠራተኞች የሚለብሱትን አይነት አለባበስ የለበሰ፣ ከወጣትነት ይልቅ በጎልማሳነት ዕድሜ ላይ የሚሆን ሰው ‹‹አዲስ ፓስፖርት ለማውጣት ነው?›› አለኝ፡፡ ‹‹አዎ!›› አልኩት፡፡ መሰለፍ ያለብኝን ቦታ አሳየኝና ተሰለፍኩ፡፡ ‹‹ባለጉዳይ ነው ወይስ አስተባባሪ ነገር!›› እያልኩ በውስጤ ሳሰላስል፤ ሌላ ከፊት ካሉ ሰልፈኞች ጋር ሥራ የሚሰራ የሚመስል ተመሳሳይ አለባበስ የለበሰ ባልደረባውን ‹‹እነዚህን አስሞላኻቸው?›› አለው፡፡ ተጠያቂውም ልክ በሥራ የተወጠረ (ቢዚ የሆነ) በሚመስል ስሜት ‹‹አዎ! አዎ!›› አለው፡፡

ሰልፉ እጅግ በጣም ረጅምና አሰልቺ ከመሆኑ የተነሳ አሰራሩን ለማፋጠን ከአሻራ በፊት አንዳንድ መፈጸም ያለባቸውን ጉዳዮች (ምናልባት ካሉ) ለማስጨረስ በሚል የተቋሙ አሰራር አካል ነው ብዬ አሰብኩ፤ ወይም በየቦታው የምናየው የተለመደው የባንክ ሰራተኞች ‹‹አካውንት ክፈቱ፣ ይህን አገልግሎት ክፈቱ...›› ይሆናል ብዬ አሰብኩ፡፡

እንዲሰለፍ የጠቆመኝ የባንክ ሰራተኛ መሳይ መጣና መጀመሪያ ስልኬን ጠየቀኝ፤ ነገርኩት፡፡ የምነግረውን የሚጽፈው ስልኩ ላይ ነው፡፡ የሚጽፍበት ቦታ (ስፔስ) የሆነ ነገር በኦንላይን ስንሞላ ያለውን አይነት ቅጽ ያለው ነው፤ ምን እንደሚል ግን ማንበብ አልቻልኩም። ቀጥሎ የኔን ስም፣ የአባቴንና አያቴን እየጠየቀኝ ሞላ፡፡ እስከዚህ ድረስ ‹‹ተገላገልኩ!›› በሚል የደስታ ስሜት ነበር እየነገርኩት የነበረው፡፡ ምክንያቱም አሰራሩን ለማፋጠን የሚደረግ ነው የመሰለኝ፡፡

ቀጥሎ የእናቴን ስም ጠየቀኝ፡፡ አሁን ነገሩ አላማረኝም፡፡ የተቋሙ የአሰራር አካል አልመሰልህ አለኝ። አሞላሉንም እየተጠራጠርኩት መጣሁ፡፡ እንዲህ አይነት ነገር ሲሞላ የፊደል አጻጻፍ (Spelling) ይጠየቃል፤ እሱ ግን አልጠየቀኝም፡፡ የሰው ስም አጻጻፍ ደግሞ እንግሊዘኛ የማወቅ ብቃት ስላለ ብቻ የሚቻል አይደለም፡፡ ለምሳሌ፤ ዋለልኝ የሚለውን የእንግሊዘኛ አጻጻፍ ብዙዎች በትክክል አይጽፉትም፡፡

ይህን እያሰብኩ የእናቴን ስም ለማረጋገጫ ነገርኩት፡፡ ምክንያቱም የእናቴ ስም ጥምር ቃል ስለሆነ በተመዘገብኩባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ለማረጋገጥ ደጋግመው ይጠይቁኛል፡፡ በተለይ በእንግሊዝኛ ሲሆን ራሴ እንድጽፈው ወይም የጻፉትን አይቼ እንዳረጋግጥ ያደርጉኛል፡፡ ይህ ሰው ግን የእናቴን ስም ስነግረው ልክ እንደሚያውቃት ሁሉ ለማረጋገጥ ሳይጠይቀኝ ስልኩ ላይ ጻፈ፡፡ ዓላማው ፎርም እየሞላ ማስመሰል ነበር ማለት ነው፡፡

እስከዚህ ድረስ በነገርኩት መረጃዎች ምንም የሚፈጠር ነገር እንደማይኖር ስላወቅኩ (የነገርኩት መረጃዎች ምሥጢራዊ ሳይሆኑ ከየትም የሚገኙ ናቸው) ከዚህ በኋላ ያሉትን በጥንቃቄ መከታተል አስቤያለሁ። ‹‹ዞር በል!›› ካልኩት ደግሞ የሰውየውን ዓላማ ለማወቅ ስለማያስችለኝ እኔም የተሸወድኩ መስዬ መከታተል ጀመርኩ፡፡

ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ ስልኬን እንድሰጠው ጠየቀኝ፡፡ እንኳን እንዲህ አይነት ቦታ ላይ ቅርንጫፍ ላይ እንኳን ቁጥሩን እንጂ ስልክ የሚቀበሉበት (ከእጅ ላይ) አሰራር በጣም አልፎ አልፎ መሆኑን ስለማውቅ፣ መስጠት እንደሌለብኝ ባምንም የተሸወድኩ መምሰል ፈልጌያለሁ፡፡ ግራ የገባኝ በመምሰል ‹‹ግን ለምንድነው?›› ብዬ ጠየቅኩት፡፡ የነገረኝን ምክንያት በኋላ ስደርስበት በፍጹም የሌለ አሰራር ነው፡፡ ‹‹በሞባይል ባንኪንግ የሚከፈል ክፍያ አለ፤ ስትጨርሱ እዚያ ጋ ትከፍላላችሁ›› ብሎ የሆነ አነስተኛ ሰልፍ ያለበት ቦታ ጠቆመኝ፡፡ ያ ቦታ በኋላ ሳረጋግጥ አስቸኳይ ፓስፖርት ለሚያወጡ ሰዎች እንጂ ከእኔ ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡

እኔም እንደ መደበሪያ አደረኩት መሰለኝ በመሃል በመሃል ስለሰልፉ እርዝመት እያወራሁ፣ ‹‹እንዲያው እስከ ስንት ሰዓት እንጨርስ ይሆን?›› እያልኩ ትኩረቴ ሰልፉ ላይ ብቻ እንዲመስል አደረኩ፡፡ ‹‹ግን እኮ ሞባይል ባንኪንግ እጠቀማለሁ፣ ቴሌብርም እጠቀማለሁ..›› አልኩት፡፡ ‹‹አክቲቭ›› የሚደረግ ነገር እንዳለ ነገረኝ፡፡ ከዚህ በኋላ ቆይታችን ሊቀጥል አልቻለም፡፡ ስልኬን እንደማልሰጠው ከሁኔታዬ አረጋገጠ መሰለኝ ስልኩን እየነካካ ወደኋላዬ ወዳለው ሰልፍ አለፈ፡፡

ይህኔ ከኋላዬ ያሉትን ሰዎች ከእናንተ ፊት ነኝ ብዬ፤ ከፊቴ ያሉትንም ከእናንተ ቀጥዬ ነኝ ብዬ መኖሬን አሳውቄ ወደ በሩ አካባቢ ፖሊስ ፍለጋ ሄድኩ፡፡ ሰውየውን ለማስያዝ ብቻ ሳይሆን ‹‹እንዲህ አይነት አሰራር አላችሁ ወይስ አጭበርባሪዎች ናቸው?›› ብዬ ለመጠየቅ ነው፡፡ በሩ አካባቢ ስደርስ ግን አንድ እንኳን ነፃ ፖሊስ ወይም አስተባባሪ የለም፤ ሁሉም የተዋከበ እና ከሰዎች ጋር የሚዳረቅ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ መጠየቅ እንደማይቻል ሳውቅ ወደ ሰልፌ ተመለስኩ፡፡

‹‹ባንኮች እንዲህ አይነት አሰራር አላቸው ወይ?›› የሚለውን ለማወቅ ባንክ የሚሰራ አንድ ጓደኛዬን ጠየቅኩት፡፡ ከሰውየው ጋር የነበረንን የመረጃ ልውውጥና ሁኔታ ስነግረው ‹‹ሲቢኢ ብር›› የሚባለውን የንግድ ባንክ አሰራር አይነት የሚመስል ሙከራ ቢኖረውም በፍጹም የባንኩ ሠራተኞች አሰራር አይደለም፡፡ ስልክ ቁጥርን እንጂ ስልክን መቀበል በፍጹም አይቻልም፤ አስፈላጊ ከሆነም ቅርንጫፍ ላይ ብቻ ነው፡፡ ሙከራው በጣም የሚያስነቃ የማጭበርበር አይነት መሆኑን ከነገረኝ በኋላ ብዙ የዚህ አይነት ገጠመኞችን ነገሮኛል፡፡ አንዱን ገጠመኝ ልጥቀስ፡፡

አንዱ አጭበርባሪ ከአንዲት ሴትዮ ዕቃ የሚገዛ መስሎ ነው፡፡ ዋጋው ከ100 ሺህ ብር በላይ ነው። መጀመሪያ ስልኳን ተቀበለ፡፡ እሱ ግን የባንክ ሠራተኛ መስሎ ሳይሆን ስልኩ ሳንቲም የዘጋበት መስሎ ነው። ጓደኛው ጋ የሚደውል በመምሰል የራሱን ስልክ ቁጥር ስልኳ ላይ CBE ብሎ መዝግቦ ሰጣት፡፡ ከዚያም ሲከራከር ቆይቶ የተስማሙበትን ዋጋ ሊከፍል ስልኩን መነካከት ጀመረ፡፡ የእሱ ስልክ ከእሷ ስልክ ላይ በንግድ ባንክ ስም ተመዝግቧል፡፡ ብር ሲገባ የሚመጣውን መልዕክት (has been Credited) ጽፎ ያስቀመጠውን መልዕክት የብሩን መጠን አስተካክሎ ላከላት፡፡ በአንዳንድ ቅጽበቶች ልብ የማይባሉ ነገሮች አሉና (ቀሪ ሂሳብም አላየችም) ተጭበረበረች ማለት ነው፡፡

እኔን ያገጠመኝ ሰውዬ ሊያደርግ የነበረው ከአካውንቴ ላይ ብር ማስተላለፍ መሰለኝ፡፡ ተቀናሽ መሆኑን የሚያሳውቀውን የባንኩን መልዕክት ስልኬን ከመስጠቱ በፊት ሊያጠፋው ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ባንኩ መልዕክት ለመላክ ይዘገያል፤ ምናልባት ሰውዬው ቶሎ ከአካባቢው ይጠፋል ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ ግን ስልክን ለመቀበል መጠየቁ የለየለት ማጭበርበር ነበር ማለት ነው፡፡

እነዚህ ሰዎች ለዚህ ዓላማ ሲሉ በር ላይ የሚታየውን አስፈላጊ ሰነዶች አሟልተው ገብተዋል ማለት ነው፡፡ እንዲህ አይነት አጭበርባሪዎች የመደበኛ አሰራሮችን ሥራ ያስተጓጉላሉ፤ መተማመን እንዳይኖር ያደርጋሉ፡፡ በእንዲህ አይነት ሰዎች ምክንያት ሁሉን ነገር ተጠራጣሪ መሆን የለብንም፤ ያም ሆኖ ግን ጥንቃቄና ሕጋዊነታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## በእስራኤልና ሐማስ መሪዎች ላይ የወጣው የእስር ትዕዛዝ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት (አይሲሲ) በእስራኤልና ሐማስ መሪዎች ላይ የእስር ትዕዛዝ ማውጣቱን ሁለቱም ወገኖች ተቃውመውታል።

የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ እሳቸውን ጨምሮ የሐማስ መሪዎች በጋዛ ግጭት ፈጽመዋል በተባለው ወንጀል ምክንያት የዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት (አይሲሲ) የእስር ትዕዛዝ እንዲወጣባቸው መጠየቁን በቁጣ አውግዘዋል።

ኔታንያሁ “ዲሞክራሲያዊት እስራኤል” “ከጅምላ ገዳዮች” ካሏቸው ጋር እኩል መፈረጇን በመጸየፍ እንደማይቀበሉትም ገልጸዋል።

የኔታንያሁን አስተያየት የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አስተጋብተውታል። በእስራኤል እና በሃማስ መካከል ምንም ዓይነት ተመሳሳይነት የለም ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ኔታንያሁ እና የመከላከያ ሚኒስትሩ ዮአቭ ጋላንት በጋዛ ለተፈጸሙ የጦር እና በሰው ልጆች ላይ ለተፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂ ናቸው ብሎ ለማመን የሚበቁ ምክንያቶች አሉ ሲሉ የአይሲሲ ዋና ዓቃቤ ህግ ካሪም ኻን ገልጸዋል።

በጋዛ የሚገኘውን ሐማስን የሚመሩት ያህያ ሲንዋር ላይም ተቋሙ በጦር ወንጀለኞች ምክንያት የእስር ማዘዣ እንዲወጣባቸው ጠይቋል።

እስራኤል እና ዋነኛ አጋሯ ዩናይትድ ስቴትስ እአአ በ2002 የተቋቋመው የአይሲሲ አባል ሀገራት አይደሉም።

በእስራኤል እና በሐማስ መሪዎች ላይ የተሰነዘረው ውንጀላ መስከረም 26 የሐማስ ታጣቂዎች በእስራኤል ላይ ጥቃት ሰንዝረው ወደ አንድ ሺህ 200 የሚጠጉ ሰዎችን ገድለው 252 ሰዎችን አግተው ወደ ጋዛ ከወሰዱበት ክስተት ጋር የተያያዘ ነው።

የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን በበኩላቸው፤ የፕሬዚዳንቱን ውግዘት “ዋሽንግተን እርምጃውን በመሠረታዊነት አትቀበልም” ሲሉ አስተጋብተዋል። “አሳፋሪ ነው። አይሲሲ በዚህ ጉዳይ ላይ ስልጣን የለውም” ብለዋል።

የእስር ማዘዣ ጥያቄው የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ ለመድረስ እየተደረገ ያለውን ጥረት አደጋ ላይ ይጥላል ሲሉም ብሊንከን ጠቁመዋል።

አይሲሲ በተጨማሪ የሐማስ መሪዎች ላይም የእስር ማዘዣ

ትዕዛዝ እንዲወጣባቸው ጠይቋል። የሐማስ መሪዎችን ማጥፋት፣ ግድያ፣ ማገት፣ አስገድዶ መድፈር እና ወሲባዊ ጥቃት እና ማሰቃየትን ጨምሮ ሌሎች ወንጀሎችን ፈጽመዋል ሲሉ ኻን ከሰዋል።

የአይሲሲ ዳኞች የእስር ትዕዛዙን በማውጣት ላይ ውሳኔ ይሰጡበታል። ትዕዛዙ ከወጣ የአይሲሲ አባል ሀገራት ሰዎቹን የማግኘት ዕድል ካላቸው በቁጥጥር ስር ያውሏቸዋል።

ለረዥም ጊዜ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን በማገልገል ላይ የሚገኙት ኔታንያሁ የእስር ትዕዛዝ እንዲወጣባቸው መጠየቁን “የማይረባ እና የውሸት ትዕዛዝ” ሲሉ አውግዘውታል።

በዕብራይስጥ ቋንቋ በተላለፈ መግለጫቸው ፍርድ ቤቱ ሐማስን እና እስራኤልን “በምን ድፍረት ለማወዳደር ቻለ” ሲሉ ጠይቀዋል። ንጽጽሩ “እውነታን ማዛባት” ነበር ሲሉ ኔታንያሁ አክለዋል።

የእስራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እስራኤል ካትስ በበኩላቸው ኻን የወሰዱትን እርምጃ በመስከረም 26 ሰለባዎችን “ማጥቃት” እና “ለዘላለም የሚታወስ ታሪካዊ ውርደት” ሲሉ ጠርተውታል።

የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሰጠው መግለጫ፤ ፍርድ ቤቱን እና “በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ያለቅጣትን መከላከል” ሲል የጠራውን ውሳኔ እንደሚደግፍ ተናግሯል።

የጀርመን ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም የአይሲሲን ነፃነት እና አሠራር እንደሚያከብር ተናግሯል።

በእስራኤል እና በሐማስ መሪዎች ላይ የተሰነዘሩ ክሶች በአንድ ጊዜ መውጣታቸው እርምጃ “ትክክለኛ ያልሆነ የተመሳሳይነት ስሜት ፈጥሯል” በማለት አስታውቋል።

ሐማስ በበኩሉ “በፍልስጤም ተቃውሞ መሪዎች ላይ የወጡት የእስር ማዘዣዎች በሙሉ እንዲሰረዙ” የራሱን ጥያቄ አቅርቧል።



**የሐማስና እስራኤል መሪዎች የእስር ትዕዛዙን ተቃውመዋል፣**



# ባለውለታዎቻችን

## ሀገር ወዳድ የእምነት አባት

ክብረአብ በላቸው

ኢትዮጵያ የብዙ ደማቆች ሀገር መሆንዋ የታወቀ ቢሆንም ታሪካቸው በአግባቡ በወረቀት ላይ ተፅፎ የተመዘገበው የጥቂቶቹ ብቻ ነው። በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችና ባገኙአቸው ዕድሎች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ዕውቀት ለመቅሰምና የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት የቻሉ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ያገኙትን ዕውቀት ለወገኖቻቸው ለማድረስና አዳዲስ አሠራርንና አስተሳሰብን በሕዝቦቿ መካከል ለማስረጽ፣ አብዝተው የደከሙና ሕይወታቸውን አሳልፈው እስከ መስጠት የደረሱ ፋና ወጊ ምሁራን እንደነበሩ ይታወቃል፡፡

ሀገራቸውን ከውጭ ወራሪና ጠላት በመከላከል አኩሪ ታሪክ የሠሩ፣ የሕዝባቸውን ደኅንነትና አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ መስዋዕትነት የከፈሉና አንፀባራቂ ታሪክ የሠሩ ጥቂቶች አልበሩም። በደራሲነት፣ በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በስፖርት፣ በታሪክ፣ በሳይንስና በእምነት አስተምሮ፣ የኪነ ጥበብና የምርምር ሥራዎችም ኢትዮጵያን በዓለም የበለጠ እንድትታወቅ ያደረጉ ትናንትናም ዛሬም ደምቀው የሚታዩ ደማቅ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብዙዎች ናቸው፡፡

ስመ ጥር ወንጌላዊና የኦሮሞ መብት ታጋይ የነበሩት ጉዲና ቱምሳ ትውልዳቸው በ1921 ዓ.ም ቦጂ ወለጋ ነው። የተለያየ እምነት ተከታይ ከነበረው ቤተሰብ የሚወለዱት ጉዲና ቱምሳ አባታቸው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት፣ እናታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ሲሆኑ ወንድማቸው ደግሞ ቃሉ ነበር።

ባለብሩህ አዕምሮ የነበሩት ጉዲና በልጅነታቸው እስከ አራተኛ ክፍል ያለውን ትምህርት ለማጠናቀቅ የፈጀባቸው ሁለት ዓመት ብቻ ነበር። ከመደበኛ ትምህርታቸው ጋር አያይዘው የወንጌልን ትምህርት መከታተል የጀመሩት ጉዲና የ5ኛ እና የ6ኛ ክፍል የትምህርት ቤት ክፍያቸውን ወጪ ለመሸፈን ሲሉም ነጆ ይገኝ በነበረው በManfred Lundgren የስዊዲሽ ሚሲዮን አንዳንድ ሥራዎችን ይሰሩ ነበር። ከዛም ለተሻለ ትምህርት ወደ ነቀምቴ በመጓዝ በነርስነት ሞያ ሰልጥነው ተመረቁ።...

ቤተሰባቸውን በሞት ሲነጠቁ ወንድሞቻቸውን ይዘው ኑሯቸውን በነቀምቴ ያደረጉት ጉዲና ቱምሳ በስዊዲሽ ኤቫንጀሊካል ሚሽን ሆስፒታል በድሬሰርነት ማገልገል ጀመሩ። በዚሁ ሥራ ላይ እንዳሉም ከባለቤታቸው ፀሐይ ቶሎሳ ጋር ጋብቻቸውን ፈጸሙ፡፡ ወትሮም ለመንፈሳዊ ትምህርት ዝንባሌ የነበራቸው ጉዲና ለአራት ዓመታት ያክል የሥነ መለኮት ትምህርት ተከታትለው ተመርቀዋል። ከዚህ በኋላ ነው ቄስነት ተክነው ቄስ ጉዲና ቱምሳ የተባሉት።

የነገረ መለኮት ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በነቀምቴና በከምባታ በፓስተርነት ሲያገለግሉ የቆዩት ቄስ ጉዲና ቱምሳ፣ በአገልግሎታቸው ትጋትና በነበራቸው ድንቅ ችሎታ የተነሳ በኢትዮጵያ ወንጌላዊ ቤተክርስቲያን መካነ-ኢየሱስ ስፖንሰርነት ወደ አሜሪካ ለላቀ የሥነ-መለኮት ትምህርት ለመማር በቅተዋል። ከአሜሪካ ከተመለሱ በኋላም የመካነ-ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ዋና ፀሐፊ ሆነው ተሹመው ነበር። ቄስ ጉዲና ከዚህ ከተሾሙበት የቢሮ ሥራቸው በተጨማሪ ወንጌልን በማስፋፋት ሥራ ላይ ትልቅ ሥራን ይሰሩ እንደነበር ይነገርላቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ቄስ ጉዲና በ1966 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የሉተራን ጉባኤ ካውንስል መስራችና ፕሬዚዳንትም ነበሩ።

ቄስ ጉዲና በደርግ ዘመነ-መንግሥት የመካነ-ኢየሱስ ቤተክርስቲያን መሪ የነበሩ ከመሆናቸውም ባሻገር፤ በወቅቱ በካቶሊክ፣ በኦርቶዶክስና በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ጥምረት ተመስርቶ የነበረው ምክር ቤት (ካውስንል)የመጀመሪያው ሊቀ መንበርም ሆነው አገልግለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አብያተ ክርስትያናት



ቄስ ጉዲና ቱምሳ፤

( የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ቤተክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን ጨምሮ) በጋራ በሆኑ ጉዳዮቻቸው ላይ አብረው የመሥራትን ራዕይ ፀንሶ የተነሳው ጉባኤ በቄስ ጉዲና ያላሰለሰ ጥረት ህልውና ያገኘ ቢሆንም ለህልፈተ ሕይወታቸው ምክንያት ከሆኑት ነገሮች መካከል ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ የመተባበር ጉባኤው መስከረም 1969 ዓ.ም ሲመሰረት ከመንግሥት ዕውቅና የጠየቀው ግን በ1971 ዓ.ም እንደነበር ሰነዶች ያወሳሉ፡፡ በመተባበር ጉባኤው ውስጥ የነበሩ የሃይማኖት ተወካዮች እንደሚናገሩት "የእውቅና ስጡን" ጥያቄው ለመንግሥት የሚዋጥለት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በወቅቱ በርካታ የውጭ መገናኛ ብዙሃን በኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ነፃነት እንደሌለና አማኞችም እየታሰሩ፤ እየተሰቃዩና እየተገደሉ እንዳለ ቢዘግቡም መንግሥት ይህን ዘገባ ለማስተባበል ከፍተኛ ጥረትና ሙከራ አድርጓል፡፡ በ1970 ዓ.ም ሁኔታውን እንዲመረምር በመንግሥት የተሰየመው ኮሚቴ የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት የሃይማኖት ድርጅት ተወካዮች በተገኙበት በአፍሪካ አዳራሽ አንድ ስብሰባ ጠራ፡፡ በስፍራው የመተባበር ጉባኤ አባላትም ተገኝተዋል፡፡

ስብሰባው የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች የቀረቡበት አካሄዱም መንግሥት በቀደደለት ቦይ የፈሰሰ ቢሆንም በመጨረሻው ተናጋሪ በቄስ ጉዲና ቱምሳ ንግግር ግን ብርቱ የሆነ ተግዳሮት ነበር የጠበቀው፡፡ ቄሱ በድፍረት በጉባኤው ላይ የተነገረው ቅጥፈት ሁሉ እንዳሳዘናቸው ከገለጹ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ እርሳቸው እስከሚያውቁት ድረስ የሃይማኖት መረገጥና የምዕመናን ስቃይ እያየለ መምጣቱን ስፍራና ቦታ ጭምር በመጥቀስ የተፈፀመውን ግፍ ሁሉ እየዘረዘሩ ባስቀመጡት መረጃ ሀቁን አወጡ፡፡ የስብሰባው አካሄድ ከታለመለት ፈር እያፈነገጠ መምጣቱ ያስደነገጠው ደርግ ሁኔታዎችን በማረጋጋት ጉባኤውን የበተነ ቢሆንም ቄስ ጉዲናን ግን በመንጋጋው ለማድቀቅ ጥርስ ውስጥ አስገባቸው፡፡

የመንግሥት አካላት ቄስ ጉዲናን በመጥራት አብዮቱን መቃወማቸውን እና ተቃዋሚ የፖለቲካ እንቅስቃሴም የሚደግፉ መሆናቸውን ከገለፁላቸው በኋላ ያም ሆኖ ከመንግሥት ጋር የሚተባበሩ ከሆነ በአንድ ዓለም አቀፍ ኃላፊነት ቦታ ላይ እንደሚመደቡ በመግለፅ ሊያግባቧቸው ቢሞክሩም እሳቸው ግን አሻፈረኝ አሉ፡፡ በአንድ ወቅት ለሴት ልጃቸው በፃፉት ደብዳቤ ላይም "ከዚህ የሰውን መብት በሰፊው ከሚረግጥ መንግሥት ጋር ከመሥራት ሞት ይሻለኛል" በማለት መግለፃቸው የአላማቸውን ጥንካሬ የሚያሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ቄስ ጉዲና የተሠውት በ1971 ዓ.ም. በሃምሳ ዓመታቸው ነው። ጽሑፋቸውን ያነበበና ንግግራቸውን ያደመጠ ማንም እንደሚያውቀው ወንጌልን ከማሕበራዊ ፍትህ ጋር አገናዝበው ማየት የተቻላቸው ግለሰብ ነበሩ። ወንጌልን ወይም የእምነት አስተምህሮን በቤተክርስቲያን ክልል ብቻ መወሰን ወይም በማህበረሰብ ጠርዝ ላይ መትከል፣ የወንጌልን "ብርሃን እና ጨው"ነት አለማጤን እንደሆነ የተረዱ መሪ ነበሩ።

ለመንግሥት ሥጋት የሆኑት ከዚህ አመለካከታቸው የተነሳ እንደሆነ ይነገራል። ስለ ሰው ማንነት ያላቸው መረዳት ከወንጌል አስተምርሆ የመነጨ እንጂ ከሰብዓዊነት አመለካከት ብቻ የፈለቀ አልነበረም። ወንጌል፣ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩን፣ ከዚህ የተነሳ ክቡር መሆኑን፣ በአዳማዊ ኃጢአት ምክንያት ከፈጣሪው፣ ከራሱ፣ ከባልንጀራውና ከፍጥረት ሁሉ ጋር መቆራረጡን ያስተምራል። ይህም ከማርክሳዊ አመለካከት፣ ብርሃን ከጨለማ እንደሚለይ ይለያል። ወንጌል፦ ሰው ቁስ ብቻ ሳይሆን፣ ነፍስም መንፈስም ነው፤ በሥጋ በተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በኩል ከአምላኩ፣ ከራሱና ከሌላው ጋር የሚታረቅበት መንገድ ተዘጋጅቶለታል ይላል። የቄስ ጉዲናና የቤተክርስቲያናቸው አስተምህሮም ይሄው ነበር።

ቄስ ጉዲና በኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች ማንበብና መጻፍ እንዲስፋፋ ከወጠኑትና ጥረት ካደረጉት መካከል የመጀመሪያው ናቸው። በተፈጥሯቸው የመሪነት ጸጋን የተላበሱትና አንደበተ ርቱዕ የነበሩት ቄስ ጉዲና በኦሮሞ የመብት ጥያቄ እንቅስቃሴ ውስጥም ጉልህ የሚባል ሚና ነበራቸው። በዚህም መሠረት መንግሥት የሃይማኖት ብዝሀነት በኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩን ለማሳየት በማቀድ ከተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት የተወጣጡ ልዑካንን ወደ አውሮፓ ለጉብኝት አዘጋጅቶ በነበረበት በ1970 ዓ.ም. አንዱ ተጋባዥ የነበሩት ቄስ ጉዲና ቱምሳ ጥሪውን ባለመቀበል ተቃወሙ። በዚህ የተነሳ ለእስር ተዳርገው ቢቆዩም ብዙም በእስር ላይ ሳይሰነብቱ ተፈተዋል፡፡

ከእስር የተፈቱት የዓለም ሉተራን ፌዴሬሽን የታንዛኒያውን ፕሬዚዳንት ጁሊየስ ኔሬሬ ደርግ ጋር ሽምግልና ልከው እንደሆነ ይነገራል ነገር ግን ደርግ ከእስር ይፍታቸው እንጂ እያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸውን በዓይነ ቁራኛ ይከታተል ነበር። በዚህ ጊዜ ቄስ ጉዲና ሀገር ለቀው እንዲወጡ ቢጠየቁም በጀ አላሉም ነበር። "...ሕዝቤ እና ቤተክርስቲያኔ እዚህ ናቸው። መንጋውን ጥዬ ወዴትም አልሄድም።" ነበር መልሳቸው፡፡ በመጨረሻም ሐምሌ 21 ቀን 1971 ዓ.ም. ደርግ ቄስ ጉዲናን ከመንገድ ላይ አፍኖ በመውሰድ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ገድሏቸዋል። በዚሁ ቀን ነበር አቡነ ቴዎፍሎስም የተገደሉት።

ቄስ ጉዲና ቱምሳ በዚህ ቀን በሥራ ተወጥረው ዋሉ፡፡ ምሽት ላይ በካዛንቺስ አካባቢ በሚገኘው ዑራኤል መካነ ኢየሱስ የወንጌል ስብከትና አስቀድሞም በዚህ ቦታ ሌሎች ተግባራትን ያከናውኑ ስለ ነበረ ዕረፍት አልነበራቸውም፡፡ የወንጌል መልዕክት አሰምተው ከቤተ ክርስቲያን ከወጡ በኋላ ወደ ቤታቸው ለመሔድ መኪናቸው ውስጥ ገቡ፡፡

ከዚያም ወደ ዋናው ጎዳና የሚያመራውን መንገድ እንደያዙ የፖሊስ መኪኖችና በርካታ የወታደር ጂፖች መንገዱን ዘግተውት እንዲያቆም አዘዟቸው፡፡ አስቁመው ወደ ሌላ መኪና እንዲገቡ ካስገደዷቸው ምሽት በኋላ ቄስ ጉዲና አልታዩም፡፡ ቤተሰቦቻቸው ቄስ ጉዲናን ለማግኘት በርካታ ጥረቶችን አደረጉ ግን አልተሳካም፡፡ የደርግ መንግሥት ከወደቀ በኋላ በተደረገ ፍለጋ ወታደር ከበደ አማረ "የአፋልጉኝ" ጥያቄውን በሬዲዮ እንደሰማ፤ የተቀበሩበትን ስፍራ ለማመልከት ከደሴ ተነስቶ መጣ፡፡ ተገድለው የተቀበሩበትን ቦታ አመልክቶ ቁፋሮው ተጀመረ አንድ ሜትር ሳይርቅ አፅማቸው ተገኘ፡፡ እንደ ከበደ አማረ አባባል፤ ቄስ ጉዲና ታፍነው በተወሰዱበት ምሽት የተገደሉት በገመድ ታንቀው ነበር፡፡

ሰኔ 21 ቀን 1984 ዓ.ም ከ13 ዓመት በኋላ የቄስ ጉዲና መገደል ይፋ ሆነ፡፡ በርግጥ እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ከመከሠታቸው ቀደም ብሎ በርካታ ወዳጆቻቸው ከኢትዮጵያ የሚወጡበትን መንገድ ያመቻቹላቸው ቢሆንም፤ በሚያገለግሉት ሕዝብ ፊት ሰማዕትነትን መቀበል መረጡ፡፡

ቄስ ጉዲናን መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን በጠንካራ እምነታቸው፣ ኦሮሞ ወንድሞቻቸው ደግሞ በመንፈስ ጠንካራነታቸው እና በቆራጥነታቸው ዛሬም ድረስ ያስታውሷቸዋል።

የቄስ ጉዲና ሴት ልጅ ወይዘሮ ሌንሳ ጉዲና ስለ ወላጅ አባታቸው ሲናገሩ፤ ልቡ ለደሃ የሚራራ ሁሉንም ሰው እኩል የሚመለከት ሰው ነበር ትላለች። "አባቴ ለሀገሩ ልዩ ፍቅር ነበረው ለእኛም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሀገር ፍቅር እንዲኖረን ሕዝባችንን እንድንወድ ይነግረን ነበር ትላለች።

ቄስ ጉዲና እየነገሩን ያደግነው በጎ ማድረግን ለሌሎች መትረፍን ነው የሚሉት ወይዘሮ ሌንሳ፤ ይህንን ራዕይ በመወሰድ ልጆቻቸው (ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን) በመመሥረት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለህብረተሰቡ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸውን ድህንነት ቅነሳ ላይ ያተኮሩ በግብርና፣ በጤናና በትምህርት መሠረተ ልማት መሟላት ላይ ትኩረት በማድረግ የሳቸውን ስም ከመቃብር በላይ ለማኖር እየሠሩ እንደሆነ ይናገራሉ።

እኛም በዚህ ለሕዝብና ሀገራቸው መልካም ያደረጉና በተሰማሩበት ዘርፍ ሁሉ የማይነጥፍ ዐሻራ ማኖር የቻሉ ግለሰቦች ታሪክ አንስተን ለአበርክቷቸው ክብር በምንሰጥበት በዚህ የባለውለታዎቻችን ዓምድ እውቁን የኢትዮጵያ መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን መሪና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች የሆኑትን ቄስ ጉዲና ቱምሳን ላበረከቱት ዘመን ተሻጋሪ ሥራ አመሰገንን።

# ስፖርት





## ስፖርትን ከቱሪዝም ያጣመረው ታላቁ የበቆጂ ሩጫ

ብርሃን ፈይሳ

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስመጥር ከሆኑ አትሌቶች መካከል በርካቶቹ የበቀሉት በቆጂ ምድር ነው፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ታዳጊና ተተኪ አትሌቶችን አሁንም እያፈራ የሚገኘው ይህ የአትሌቲክስ ማዕከል የአየር ሁኔታው፣ የቦታ አቀማመጡ እንዲሁም የሕዝቡ አኗኗር ሁኔታ ለስፖርቱ ምቹ በመሆኑ አትሌቲክስን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ እንዲኖር አድርጎታል፡፡

‹‹የሯጮቹ ምድር›› በሚል ስያሜ የሚታወቀው በቆጂ በዓለም አቀፉ የአትሌቲክስ ቤተሰብ ዘንድ በስፋት የሚታወቅና የሚጎበኝም ጭምር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስፍራው በሚገባው ልክ ያልተሰራበት አትሌቶችና ነዋሪዎቹም የሚገባቸውን ጥቅም ያላገኙበት ነው፡፡

ይህንን ተከትሎም የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚኒስቴር ከታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በየዓመቱ የታላቁ በቆጂ ሩጫን በማዘጋጀት የስፖርት ቱሪዝምን ለማስፋፋት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ለየትኛውም የስፖርት ዓይነት ምቹ የሆነ የአየር ሁኔታ እንዲሁም መልክዓ ምድራዊ ሀብት ያላት ኢትዮጵያ በዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ሳታገኝ ቆይታለች፡፡ በመላው ዓለም በፍጥነት እያደጉ ካሉ ዘርፎች መካከል አንዱ ስፖርት ቱሪዝም ሲሆን፤ ውድድሮችን በማዘጋጀት፣ ስታዲየሞችንና የስፖርት ማዘውተሪያዎችን በመገንባት እንዲሁም በስፖርቱ አዝናኝና ሳቢ ክንውኖችን በማሰናዳት በርካታ ሀገራት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ እንደ ታላቁ ሩጫ ያሉ ስፖርታዊ ተቋማት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዘርፉ ያለውን ሁኔታ በማነቃቃት ላይ ይገኛሉ።

ነገር ግን ኢትዮጵያ ባላት ሀብት ልክ ተጠቃሚ ልትሆን አለመቻሏን እንደ በቆጂ ካሉ ተሞክሮዎች



የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ፤

መረዳት ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ ስም በበጎ እንዲነሳ ካደረጉ ጉዳዮች መካከል ቀዳሚው የአትሌቲክስ ስፖርት ነው፤ አትሌቲክስ ሲነሳ ደግሞ በቆጂ የማትዘነጋ ስፍራ ናት፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ መድረኮች ተሳትፎዋ ከሰበሰበቻቸው 58 ሜዳሊያዎች መካከል 18 የሚሆኑት (10የወርቅ፣ 3 የብር እና 5 የነሐስ) ሜዳሊያዎችን ያስመዘገቡ የኮከብ ሯጮች ምድር በቆጂ ባፈራቻቸው አትሌቶች በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት በአጠቃላይ በመድረኩ ከተመዘገቡት 23 የወርቅ ሜዳሊያዎች መካከል የ10 መነሻ ከአዲስ አበባ ከተማ 220 ኪሎ ሜትር ላይ የምትገኘው በተራሮች የተከበበችውና ለምለሟ በቆጂ ናት፡፡ ከሩጫ ባለፈ እንደ ብስክሌት እና ተራራ መውጣት ላሉ ስፖርቶችም በእጅጉ አመቺ መሆኗን ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡

በታላቁ ኦሊምፒክ በሴቶች ዘርፍ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ያስገኘችው አትሌት ደራርቱ ቱሉ፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ ፋጡማ ሮባ፣ እጅጋየሁ ዲባባ፣ ገንዘቤ ዲባባ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ታሪኩ በቀለ፣ ቲኪ ገላና፣ መስታወት ቱፋ፣ ትዕግስት ቱፋ፣ ለሜቻ ግርማ፣... የመሳሰሉት የኦሊምፒክ፣ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና እንዲሁም ሌሎች የአትሌቲክስ ቻምፒዮን የሆኑ አትሌቶች ከዚችው መንደር ነው የተገኙት፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚኒስቴር ስፍራውን የአትሌቲክስ እና የስፖርት ቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ ‹‹ታላቁ የበቆጂ ሩጫ›› በሚል የሩጫ ውድድር በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ዘንድሮም ለ3ኛ ጊዜ በመጪው እሁድ ግንቦት 18/2016 ዓ.ም ውድድሩ የሚደረግ ሲሆን፤ 1ሺ500 የሚሆኑ ተሳታፊዎች ይወዳደራሉ ተብሎ ይጠበቃል። በተጨማሪም የአትሌቲክስ ወዳድ የሆነውን ነዋሪ ጨምሮ ጀማሪና ታዋቂ አትሌቶች ይሳተፉበታል፡፡

የሩጫ መርሀ ግብሩን ተከትሎም የቱሪዝም ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ፤ ሩጫው የሀገር ውስጥና የስፖርት ቱሪዝምን ለማሳደግ ከማስቻሉ ባለፈ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶችንም ለመሳብ የሚጠቅም መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ከስፖርታዊ ሁነቱ ባለፈ ሌሎች የዞኑን የቱሪዝም ሀብትና ባህሎች ለማስተዋወቅም ጠቀሜታ አለው፡፡ ለዚህም የቱሪዝም ሚኒስቴር ፣ ከተማ አስተዳደሩ እንዲሁም ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቃቸው ታውቋል፡፡ ለአትሌቶች ምቹ በሆነው ምድር በሚዘጋጀው የበቆጂ ሩጫ ላይ ታዋቂ አትሌቶች ጭምር ተሳታፊ እንዲሆኑና እንዲጎበኙም አዘጋጆቹ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የበቆጂ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ብርሃኔ ነገሰ፤ በቆጂ ከሯጮች መፍለቂያነቷ ባለፈ በርካታ የተፈጥሮና ባህላዊ የሆኑ ቱሪስቶችን መሳብ የሚችሉ ሀብቶች ያላት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የበቆጂን ታሪካዊ ስፍራነት ለማሳየት እንዲሁም ይበልጥ እንዲታወቅ ለማድረግ ለሚካሄደው ሩጫ አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉንም አክለዋል፡፡ ሩጫው ወደፊትም የሀገርን ሰንደቅ የሚያጎሉ ተተኪ አትሌቶችን ለመፍጠር ከመፍጠሩም ባለፈ በቱሪዝም እንዲሁም በከተማዋ ኢንቨስት እንዲያደርግ የሚጋብዝ በመሆኑ ሁሉም የራሱን ተሳትፎ እንዲያደርግም መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡


## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2016 በጀት ዓመት የኮምፒውተርና ተዛማጅ ዕቃዎች ለሁለተኛ ጊዜ በዘርፉ ህጋዊ ፈቃድ ካላቸው ድርጅቶች አወዳድሮ በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መግዛት ይፈልጋል፡፡

1. ተጫራቾች በዘርፉ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው፣ በአቅራቢዎች ዝርዝር ድረ-ገጽ (eGP) የተመዘገቡ፤ የማጭበርበር ድርጊት ላለመፈፀም ቃል የሚገቡበት ቅፅ ላይ ማህተምና ፊርማ የተደረገበት፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ መሆናቸውን፤ የዘመኑን የሥራ ግብር የከፈሉና የግብር ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ የድጋፍ ደብዳቤ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ የሚችሉ ሆነው ሁሉንም ሠነዶቻቸውን ፎቶ ኮፒ በማድረግ እና የድርጅታቸውን ማህተም በማሳረፍ ከጨረታ ሰነዱ ጋር በፖስታ በአግባቡ አሽገው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የማይመለስ ብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስም 1000013099522 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገንዘቡን ገቢ በማድረግ ገቢ ያደረጉበትን የባንክ ደረሰኝ ከዩኒቨርሲቲው ፋይናንስ ክፍል የገቢ ደረሰኝ በማስቆረጥ የጨረታ ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡
3. የጨረታ ሰነዱን ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጥበብ ሕንፃ ማዕከላዊ ግዥ ክፍል G+2 ቢሮ ቁ-201 መግዛት ይችላሉ።
4. ማንኛውም ተጫራች ለኮምፒውተርና ተዛማጅ ዕቃዎች ግዥ፣ የጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ብር 400,000.00 /አራት መቶ ሺህ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ፣ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ ቢድ ቦንድ ጋራንቲ ወይም በጥሬ ገንዘብ ማቅረብ ለሚፈልጉ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስም 1000013099522 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገንዘቡን ገቢ በማድረግ ገቢ ያደረገበትን የባንክ ደረሰኝ ከዩኒቨርሲቲው ፋይናንስ ክፍል የገቢ ደረሰኝ በማስቆረጥ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አሽጎ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት በአዋጅ መሠረት የተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ከአደራጃቸው ተቋም በጨረታ ማስከበሪያ የዋስትና ደብዳቤ ማስረጃ ዋናውን ደብዳቤ የሚወዳደሩበትን ሎት እና የብር መጠን በመጥቀስ ያለ ክፍያ በነፃ የጨረታ ሰነዱን እና የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ማግኘት ይችላሉ፡፡
6. አሸናፊው ድርጅት ያሸነፈባቸውን ዕቃዎች አሸናፊነቱ ታውቆ ውሉ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በውሉ መሠረት ማቅረብ የሚችል መሆን ይጠበቅበታል፡፡
7.ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ በመግለፅ ፖስታ ውስጥ አድርገው ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ቀናት ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጥበበ ሕንፃ ማዕከላዊ ግዥ ክፍል G+2 ቢሮ ቁ-201 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡፡

* የኮምፒውተርና ተዛማጅ ዕቃዎች ግዥ፣- ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ16ኛው ቀን በ4፡00 ሰዓት ታሽጐ በዚሁ ቀን በ4፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡

* ማሣሰቢያ፡- ጨረታው የሚከፈትበት ቀን ቅዳሜ እና እሁድ ወይም ካላንደር የሚዘጋው ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሣሣይ ሰዓት ይሆናል።

8. በሌላ ተጫራች ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይቻልም፡፡
9. ዩኒቨርሲቲው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0583202052 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡

### ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ጥበብ ግቢ)